# አንድ አገር ሊወድቅና ሊነሳ የሚችለው፣ ወይም ደሃና ጠንካራ አገር የሚሆነው መንግስት ተግባራዊ በሚያደርገው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት ነው !!

September 4, 2018

*ፈቃዱ በቀለ(ዶ/ር)*

*መስከረም* ***02 ፣ 2018***



ፈቃዱ በቀለ (ዶ/ር)

***Human dignity is offended when persons are denied the opportunity to participate in their own development, when development "takes place over their heads."( Yuengert M. Andrew, What is "Sustainabel Prosperity for all" in the Catholic Social Tradition ? in:  The True Wealth of Nations- Catholic Social Thought and Economic Life. (Oxford, 2010)***

## መግቢያ

አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ነፃነትን ከተቀዳጁ ከሃምሳ ዓመት በኋላ በድህነት ዓለምና በጥገኝነት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በአብዛኛዎቹ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የተትረፈረፈ የጥሬ ሀብትና እንዲሁም ለነዳጅ የሚሆን ዘይትና ጋዝ ቢኖርም ህዝቦቻቸው በድህነት ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። መሬታቸው በጣም ለምለም የሆኑና ብዙ ውሃ ቢኖራቸውም ገበሬዎቹ ከእጅ ወደ አፍ በሚሆን የእርሻ ምርት ላይ የተሰማሩ ናቸው። በዚህም ምክንያት የተነሳ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከውጭ ስንዴና ሌሎች ለምግብ የሚሆኑ የእርሻ ውጤቶችን ያስመጣሉ። ወደ ደቡቡ የአፍሪካ ክፍል ስንሄድ ደግሞ በአብዛኛዎቹ አገሮች ውስጥ፣ ሞዛምቢክ፣ አንጎላ፣ ዚምባብዌና ደቡብ አፍሪካ ዋናው ምግባቸው በቆሎ ነው። መሬታቸው፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ማሽላና ዘንጋዳ፣ እንዲሁም ሌሎች ሰብሎችንና ጥራጥሬዎችን አያበቅሉ ይመስል ህዝቦቹ በቆሎን ብቻ በማምርትና ዋናው ምግባቸው በማድረግ የተመጣጠነ ምግብ(Diet) እንዳያገኙ ሆነዋል። በተለይም የቅኝ ገዢዎች የእነዚህን አገሮች የአስተራረስና የአመጋገብ

ዘዴ በማበላሸትና፣ መሬቱ በቆሎና ትምባሆ ብቻ እንዲያመርት በመደረጉ መሰረታዊ የእርሻ ባህል እንዳይስፋፋ ሆኗል። በዚህም ምክንያት የተነሳ አብዛኛው ህዝብ ዕውነተኛ የሆነ የአስተራረስ ባህል እንዳያዳብርና የተመጣጠነ የምግብ ዐይነት እንዳያገኝ ተደርጓል።

አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች የፖለቲካ ነፃነትን ከተቀዳጁ እ.አ ከ 1960 ዓ.ም ጀምሮ የገበያ ኢኮኖሚ የሚባለውን ፖሊሲ በተከታታይ ተግባራዊ ቢያደርጉም ሰፋ ያለ በስራ-ክፍፍል ላይ የተመሰረተና፣ እርስ በእርሱ ወደ ተያያዘና ግልጽ ወደ ሆነ የገበያ ኢኮኖሚ ሊሸጋገሩ አልቻሉም። ሁሉም የአፍሪካ አገሮች፣ ኢትዮጵያንም ጨምሮ በመጀመሪያ ደረጃ የምትክ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ (Import Substitution Industrialization) የሚባለውን፣ ቀጥሎ ደግሞ „መሰረታዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ" የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣(Basic Needs Economic Policy)ከዚያ በኋላ የተቀየም ማስተካከያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ(Structural Adjustment Economic Policy) ተግባራዊ ቢያደርጉም ከድህነትና ከልመና ሊላቀቁ በፍጹም አልቻሉም። ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሙሉ በዕዳ የሚተበትቧቸው፣ የንግድ ሚዛናቸውን የሚያዛቡባቸው፣ በአንድ ወይም በሁለት የጥሬ ሀብት ብቻ እንዲመኩ የሚያደርጓቸው፣ በተጨማሪም ወደ ውስጥ የማምረት ኃይላቸውን የሚያዳክሙና፣ በዚህም የተነሳ ከሰፊው ህዝብ ጋር የማይመጣጠን የፍጆታ አጠቃቀም እንዲስፋፋ በማድረግ አሁንም ቢሆን ህዝቦቻቸው ሰፋ ባለና አስተማማኝ በሆነ የኢኮኖሚ መሰረት ላይ እንዳይመረኮዙ ተደርገዋል።

በአንዳንዶች፣ በተለይም ክስተታዊ(Empiricist) የፖለቲካ አመለካከት ካላቸውና፣ የኒዎ-ክላሲካልንና የኒዎ-ሊበራልን ርዕዮተ-ዓለምን በሚያራምዱ ተንታኞች ዕምነት ለዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ቀውስና አገሮች መዝረክረክና ሀብት መባከን ዋናው ምክንያት አምባገነናዊ አገዛዞች ስልጣን በመያዛቸው ነው። ከአገራቸውና ከህዝባቸው ይልቅ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ጥቅም ያስቀድማሉ የሚል ቀላል ምክንያት ይሰጣሉ። የአፍሪካን አገሮች የተወሳሰቡ ችግሮች በዚህ ዐይነቱ ሳይንስ-አልባ አቀራረብ መረዳት በፍጹም አይቻልም። የችግሩን ጥልቀትና ውስብስብነት መረዳት የሚቻለው ከህብረተሰብ አገነባብ ታሪክ፣ ከንቃተ-ህሊና መዳበርና አወቃቀር ጋር የተያያዘና፣ በተለይም ደግሞ የውጭ ኃይሎች በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የተጫወቱትን አሉታዊ ሚናና እስካሁን ድረስ ተግባራዊ የሆኑትን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከቁጥር ውስጥ ያስገባን እንደሆን ብቻ ነው።

- የሌሎችን የአፍሪካ አገሮችንና የአገራችንን የህብረተሰብና የኢኮኖሚ ቀውስ ከቀላል ፎርሙላ ባሻገር በማየት ጠለቅ ያለ ሳይንሳዊ ትንተና ለመስጠት ካልቻልንና መፍትሄም ለመስጠት የማንሞክር እስከሆነ ድረስ በግልጽ የሚታየው ችግር ከመቶና ከሁለት መቶ ዐመት በኋላም በተመሳሳይ ሁኔታ ወይንም ከዚህ በተበላሸ መልክ ሊገኝ እንደሚችል ማወቁ ብዙም ሳይንሳዊ ምርምር የሚያስፈልገው አይመስለኝም። ስለሆነም የማንኛውም ምሁር ታሪካዊ፣ ሞራላዊ ግዴታና ኃላፊነት መሰረታዊ ችግሩንና አነሳሱን በመረዳት የተሟላና ሳይንሳዊ መፍትሄ ለመስጠት መቃጣት እንጂ፣ ቁንጽል አስተሳሰብን በማስፋፋት ሰፊውን ህዝብና፣ በተለይም ደግሞ ወጣቱን ትውልድ ማሳሳት መሆን የለበትም። ከዚህ በመነሳት አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮችንና የተሳሰቱ ፅንሰ-ሃሳቦችን ግልጽ ለማድረግ እሞክራለሁ።

ከፖሊሲ በፊት መቅደም ያለበት ጉዳይ **!!**

በሶሻል ሳይንስ ትምህርት ውስጥ የአንድን ህብረተሰብ የማቴሪያል ሁኔታ፣ የፖለቲካና መንግስታዊ አወቃቀር፣ የህዝብን የአኗኗር ሁኔታና፣ በአጠቃላይ ሲታይ የኢኮኖሚ አወቃቀርን ጉዳይ (Economic Structure) ለመመርመርና ለመረዳት የሚያግዙን የዕውቀት መሳሪያዎች አሉ። የመጀመሪያው አንድን ነገር ወደ ውስጥ ገብቶና በተለያዩ ነገሮች መሀከል ያለውን መተሳሰርና፣ አንደኛው በሌላው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ መሆኑን መመርመሪያ መሳሪያ ነው። ስለሆነም የአንድን ነገር ወይም ችግር ዋና ምክንያት ወይም ምንጭ ወደ ውስጥ ገብቶ ለመርመርና ለመረዳት የሚያስችል ሲሆን፣ በአንደኛው ክፍል ላይ የሚከሰት ችግር የግዴታ በሌሎች ክፍሎችም ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ወይም ሆኔታዎች እንዲበላሹ ያደርጋል።

- ለምሳሌ በአንድ አገር ውስጥ ስልጣንን የጨበጠው ኃይልና መንግስት ንቃተ-ህሊናው(Consciousness) በጣም ዝቅተኛ ከሆነ የሚመራበትን የህብረተሰብና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመረዳት አይችልም። በዚህም ምክንያት የተነሳ የሚያወጣቸውና ተግባራዊ የሚያደርጋቸው የማህበራዊና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ቀርቶ ህብረተሰቡን በሚያዘባራርቁ የንግድና የአገልግሎት መስኮች ላይ በመረባረብ የአገርን ዕድገት ያዛንፋል፤ ህብረተሰብአዊ ሚዛንም እንዳይኖር ያደርጋል። ይህም ማለት አንድ መንግስት በሳይንስና በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ከሌለው ሌሎች ፖሊሲዎቹ ሁሉ እንደዚሁ ፍልስፍናና ሳይንስ-አልባ ይሆናሉ ማለት ነው። በአጭሩ በዚህ የኢኮኖሚ ፍልስፍና መሰረት የአንድ አገር ችግር በተናጠል

መታየት ያለበት ሳይሆን ሁለንታዊ በሆነ መልክ ብቻ ሲሆን፣ አፈታቱም ሁሉኑም ነገር የሚያካትትና በዕውቀት ኃይል ብቻ የሚፈታ ነው። የንቃተ-ህሊና ጉዳይን ስንመለከት በጭንቅላታችን ውስጥ አንድ ቦታ ላይ የተቀመጠ ሳይሆን፣ በልምድና፣ አንድ ህብረተሰብ ውስጥ በሚገኙ የማቴሪያል ሁኔታዎችና ባህሎች ሊቀረጽ የሚችል ሲሆን፣ በተራ የአካዴሚክስ ዕውቀት ሊገኝ እንደማይችል የኳንተም ቲዎሪ፣ የኖይሮ ባዮሎጂስት ተመራማሪዎችና ፈላስፋዎች ያስረዳሉ። ስለሆነም የንቃተ-ህሊና መዳበርና አለመዳበር የአንድን አገር በሁሉም አቅጣጫ ማደግና ወደ ኋላ-መቅረት የሚወሰን ጉዳይ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ፣ አንድን ነገር ከውጭው በመመልከት ብቻ መገምገምና መረዳት የሚቻልበት መሳሪያ ነው። በዚህ ዐይነቱ ፍልስፍና መሰረት የሰው ልጅ ጭንቅላት እንዳልተጻፈበት ነጭ ወረቀት(Tabula Rasa) ሲሆን፣ አንድ ሰው የሚቀስመው ዕውቀት በምርምር ላይ የተመሰረተና ከሁሉም አቅጣጫ የሚገመገም ሳይሆን ከውጭ የሚመጣለትን የሚስብ ብቻ ነው። በዚህ ዐይነቱ የዕውቀት ዘርፍ የሰለጠነ ሰው መጠየቅና መተቸት አይችልም። የተሰጠውን ብቻ ዝም ብሎ በመሸምደድ ተግባራዊ የሚያደርግ በመሆኑ የአንድን ህብረተሰብ ችግር ዋና ምክንያት ለመመርመር አይችልም።

- የአንድን ችግር ዋና ምክንያት ለመረዳት በቁጥር የሚለኩ ነገሮችን ብቻ በመውሰድና ከዚያ በመነሳት በአንድ መስክ የተከሰተውን ቀውስ መተንተንና መፍትሄም ለመስጠት መጣር አለበት። ይህንን ዐይነት የአሰራር ስልት በሚከተሉ ምሁራን ዕምነት መሰረት በፖለቲካ፣ በመንግስትና በሌሎች ህብረተሰብአዊና ማህበራዊ ጉዳዮች መሀከል ግኑኝነት ስለሌለ፣ ለምሳሌ ፖለቲካው በኢኮኖሚውና በማህበራዊ መስክ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር አይችልም። ስለሆነም መስተካከል ያለበት ጉዳይ የፖለቲካው ጉዳይና መንግስት የሚመራበት ፍልስፍናና ሳይንስ ሳይሆኑ፣ የኢኮኖሚው ፖሊሲ ብቻ ነው። በአጭሩ ሌሎች ነገሮች እንዳሉ ሆነው ኢኮኖሚው ለገበያ ተዋንያን ከተተወ ገበያው በሂደት ውስጥ ሚዛናዊ በመሆን በኢኮኖሚ መስክ ላይ የሚታዩ ችግሮች በሙሉ፣ ለምሳሌ እንደስራ-አጥ ችግሮች በቀላሉ ሊቀረፉ ይችላሉ ይለናል።
- ወደድንም ጠላንም፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በአጠቃላይ ሲታይ በዓለም አቀፍ ደረጃና በየአገሮች ውስጥ የሚካሄዱት ትግሎች በእነዚህ ሁለት የሳይንስ ፈለግ ዙሪያ ነው። በተለይም በኢኮኖሚክስ ትምህርት የሰለጠኑ ምሁራን ሳያውቁት የሁለተኛው ሳይንስ መሰል ሰለባ በመሆን የብዙ አገሮችን ወይም ህብረተሰቦችን ዕድል ወሳኝ በመሆን ለድህነትና ለአገሮች መዝረክረክ፣ እንዲሁም በውጭ ኃይሎች ተፅዕኖ ስር መውደቅ ምክንያት ሊሆኑ ችለዋል።

  በተለይም በአለፉት አርባ ዐመታት በኢምፐሪሲዝም አመለካከት ላይ የሚመረኮዘው የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአሸናፊነት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮና የሁሉንም አገሮች ዕድል የሚወስን ዓለም አቀፋዊ አገዛዝ (World Governance) ከተመሰረተ ወዲህ እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉት እጅግ ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች የሚከተሉት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሳይንስንና የቴክኖሎጂ ዕድገትን የሚቀናቀነውን የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲን ነው። በኒዎ-ሊበራል ምሁራን ዕምነት የእያንዳንዱን አገር ችግር ከታሪክ፣ ከባህልና ከሌሎች ልምዶች አኳያ ማየትና መመርመር አያስፈልግም። የገበያ ኢኮኖሚ ከነዚህ ነገሮች ባሻገር መታየት ያለበት እንደመሆኑ መጠን፣ በሁሉም አገሮች ውስጥ ተግባራዊ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው።
- የገበያ ኢኮኖሚ እንደሂደት የሚታይና ከታች ወደ ላይ እያደገና እየተወሳሰበ የሚመጣና አንድን ህብረተሰብ የሚያዳርስ ሳይሆን ያለና ዘለዓለማዊነት ያለው ነው። ይህ ዐይነቱ ተራ የገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አመለካከት በየትምህርትቤቱ በመሰጠቱና በዓለም አቀፍ ደረጃም በመስፋፋቱ ወደድንም ጠላንም ብዙም ሳናወጣና ሳናወርድ ሁላችንም የዚህ ዐይነቱ የተሳሳተ ፖሊሲ ሰለባ በመሆን አገርን ገንቢ ከመሆን ይልቅ አፍራሽ ለመሆን ችለናል ብል የምሳሳት አይመስለኝም። ከዚህ ባሻገር ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተስፋፋው የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲን የሚያራምዱ ምሁራንና ፖሊሲ አውጭዎች ሌሎች ተወዳዳሪና ከሱ የተሻሉ የኢኮኖሚ ቲዎሪዎችና ፖሊሲዎች እንዳሉ በፍጹም ሊቀበሉ አይፈልጉም። በእነሱ ዕምነት በሌሎች ምሁራን ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ የዳበሩ ሳይንሳዊ የኢኮኖሚ ሊትሬቸሮች ተቀባይነት የላቸውም።
- በዚህ መልክ የካቶሊክ ሃይማኖት በማዕከለኛው ክፍለ-ዘመን የበላይነትን በተጎናጸፈበት ዘመንና ሳይንስንና ፍልስፋናን አጥብቆ እንደተዋጋውና የጨለማውን ዘመን እንዳራዘመው ሁሉ፣ በአሁኑ ዘመን የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚክ ፖሊሲ አራማጆችም ሌሎች የኢኮኖሚ ቲዎሪዎችንና ፖሊሲዎችን አጥብቀው በመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ድህነትና ድንቁርና እንዲስፋፋ እያደረጉ ነው። የሶስተኛው ዓለም አገሮች፣ በተለይም የአፍሪካ አገሮች አገዛዞች የኒዎ-ሊበራልን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጫና በማድረግ ወደ ውስጥ ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲፈጠርና ሀብት ወደ ወጭ እንዲወጣ በማድረግ ሰላም እንዳይሰፈን ምክንያት ሊሆኑ ችለዋል።

ያም ተባለ ይህ አንዳች ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በአንድ አገር የኢኮኖሚ አወቃቀር ላይ፣ በማህበራዊና በባህላዊ ጉዳዮች ላይና፣ እንዲሁም በአካባቢና በፖለቲካ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ጉዳይ ነው። እንደ ፖሊሲው ዐይነት አንዱ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ሊጎዳ ይችላል።

- በዚህም ምክንያት የተነሳ ማህበራዊ ውዝግቦች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲ የአንድን ህብረተሰብ ችግር ለመቅረፍ ተብሎ መነደፍ ያለበት በመሆኑ የቀውሱን ምክንያት ከሁሉም አቅጣጫ መመርመር ያስፈልጋል። የቀውሱን ወይም የበሽታውን ዋና ምክንያት በበቂው ሳይመረምሩ የሚወጡና ተግባራዊ የሚሆኑ ፖሊሲዎች ለችግሩ መፍትሄ ከመሆን ይልቅ ጥልቀት በመስጠት እንዳይፈታ ያደርጉታል። በሌላ ወገን ደግሞ ከውጭ የሚመጣን ፖሊሲ በጭፍኑ ተግባራዊ የሚያደርጉ መንግስታት ተስፋ የሚያደርጉት ነገር አለ። ይኸውም ኢኮኖሚውን በማሳደግ እንደስራ-አጥ የመሳሰሉትን ችግሮች ለመቅረፍ እንችላለን ብለው ያምናሉ ወይም ይገምታሉ። እስካሁን ድረስ እንደተረጋገጠው ይህ ዐይነቱ የየመንግስታቱ ተስፋ ከዕድገት ይልቅ ወደ ተወሳሰበ ችግርና ወደ ጥገኝነት እንደከተታቸው እንመለከታለን።
- በአለፉት ሰላሳና አርባ ዐመታት የተለያየ ስም እየተሰጣቸው በአፍሪካ ምድር ውስጥ ተግባራዊ የሆኑትን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ስንመለከትና በምድር ላይ ያለውንም ተጨባጭ ሁኔታ ስንመረምር አንድም የአፍሪካ አገር በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ሰፋ ያለ ገበያ እንዳልገነባ እንመለከታለን። በኢኮኖሚ ፖሊሲ ውስጥ ያለውን አወዛጋቢ ሁኔታ ለመረዳት በንፅፅር(Analagoy) መልክ እያወዳደሩ መመልከቱ የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲን አወዛጋቢነት እንድንገነዘብ ይጠቅመናል።

አንድ ሰው አሞት ሃኪም ቤት ሲሄድ አንድ ተስፋ የሚያደርገው ነገር አለ። ይኸውም ሃኪሙ ከበሽታዬ ይፈውሰኛል ብሎ በማሰብ ወይም በመገመት ነው። ሃኪሙም በሽተኛውን በሚገባ ሳይመረምር ዝም ብሎ መድሃኒት አያዝለትም ወይም ህክምና አያደርግለትም። መድሃኒት ከማዘዙ በፊት ምን እንዳመመውና የትስ ቦታ ላይና ከመቼ ጀምሮ በሽታ እንደሚሰማው ይጠይቀዋል። ከዚያ በኋላ በዝርዝር የህይወት ታሪኩንና፣ ከአባቱም ሆነ ከእናቱ የወረሰው በሽታ እንዳለ ይጠይቀዋል። ቀጥሎም በልጅነቱ በበሽታ ይጠቃ አይጠቃ እንደነበር፣ አሞት ከነበረ የበሽታውን ዐይነት ለማወቅ ይፈልጋል። በተጨማሪም በጊዜው ምን ዐይነት ህክምና እንደተደረገለትና፣ ከበሽታው ተፈውሶ እንደሆነ ለመስማት ይሻል። በመቀጠልም ስለአኗኗሩ፣ ስለ አመጋገቡና፣ አልክሆል ይጠጣ አይጠጣ እንደሆነ ወይም ደግሞ ሲጋራ ያጨስ አያጨስ እንደሆን ይጠይቀዋል። ከዚህም ባሻገር ስፖርት ይሰራ ወይም አይሰራ እንደሆን ጥያቄ ያቀርብለታል። በዚህ መልክ በዝርዝር ከጠየቀ በኋላ በመሳሪያው ይመረምረዋል። እንደ አስፈላጊነቱና እንደበሽታው ዐይነት የሰገራ፣ የሽንትና የደም ምርመራ ያደርጋል። ይህንን ሁሉ አድርጎ በሽታው ከሱ አቅም በላይ ከሆነ ወደ ሌላ ስፔሺያሊስት ጋ ይልከዋል። በዚህ መልክ ብቻ ነው አንድ ሀኪም ወይም ሀኪሞች ለበሽተኛው አስፈላጊውን ህክምና የሚያደርጉለት።

ወደ አንድ አገር ወይም ህብረተሰብ ሁኔታ ስንመጣም አንዳች ዐይነት ፖሊሲ ከመውጣቱ ወይም እንደመፍትሄ ከመቅረቡ በፊት የሚመለከተው አገር ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰብአዊ አወቃቀር መሰረታዊ በሆነ መልክ መመርመር አለበት። በተጨማሪም ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ወይም የተደራጁ የሙያ ማህበሮች ጋር በበቂው መወያየትና መከራከር ያስፈልጋል። ሁሉም ተዋንያን ኃይሎች ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅም ሆነ ለመረዳት የፖለቲካው አወቃቀር፣ የመንግስታዊ መኪና አወቃቀር፣ የሀብት ይዞታና የሀብት ክፍፍል ጉዳይ፣ የመዋዕለ-ነዋይ ክንዋኔና በዚህ ውስጥ የሚሳተፉ በየደረጃው ያሉ የኢኮኖሚ ተዋንያን ሁኔታና ችሎታ፣ እንዲሁም የዕውቀት ጉዳይ፣ የኢኮኖሚው መሰረት፣ ማለትም ቴክኖሎጂያዊና የኢንዱስትሪ ጉዳይ ወይም የእርሻ መስኩ ጉዳይ፣ በየመስኩ ተሰማርቶ የሚሰራው የሰው ኃይል ጉዳይ፣ በአንድ አገር ውስጥ ያለው የኢንዱስትሪዎች ዐይነትና ስርጭት፣ በከተማና በገጠር ያለው ሁኔታ፣ .... ወዘተ. ለምርምርና ለውይይት እንዲሁም ለክርክር መቅረብ አለባቸው። ከዚህም ባሻገር የህዝቡ አኗኗር፣ ማለትም የቤት አሰራር ጉዳይ፣ የከተማዎችና የመንደሮች አገነባብ ጉዳይ፣ የቆሻሻ ፍሳሽና የጽዳት ጉዳይ፣ እነዚህ ሁሉ መጠናትና በደንብ መመርመር አለባቸው።

ምክንያቱም ማንኛውም የኢኮኖሚ ፖሊሲና እንቅስቃሴ ከሰው ህይወት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ መጠንና፣ በቦታና በጊዜ(Space and Time) ውስጥ የሚካሄድ እንደመሆኑ መጠን አንድ አገር ለኢንዱስትሪ ተከላና ለሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚያመች የከተማ አገነባብና የመገናኛና የመመላለሻ አወቃቀሮች ይኖራት አይኖራት እንደሆን በሰፊው መጠናት አለበት። ከዚህም ባሻገር ጠለቅና የተወሳሰበ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚታይ ከሆነና አብዛኛው ህዝብ በድህነት የሚኖር ከሆነ በየጊዜው ተግባራዊ የሚደረጉት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ለምን ህብረተሰብአዊ ሀብት ሊፈጥሩ አልቻሉም? ድህነትን ለመቅረፍ አልቻሉም? ሰፋ ያለ የስራ መስክም ሊከፍቱ አልቻሉም? ብሎ መጠየቅና በቂ ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ከመሆኑ በፊት

ዝም ብሎ በጭፍን ተግባራዊ የሚሆን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንድን አገር ሊወጣው የማይችለው ቀውስ ውስጥ ነው የሚከተው።

ይህ ብቻ ሳይሆን አንድ መንግስት ተግባራዊ የሚያደርገው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በምድር ላይ ከሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊጣጣም የሚችልና፣ ተግባራዊ በሚሆንበትም ጊዜ ሊያስከትል የሚችለውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት በሚገባ መጠናት አለበት። ይህንንም በንፅፅር(Analagoy) እንመልከተው። ለምሳሌ አንድ መሬት ላይ አንድ ዘር ከመዝራታችን በፊት መሬቱ ያንን የዘር ዐይነት ይቀበል አይቀበል፣ አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ-ነገሮች ይኑሩት አይኑሩት በሚገባ መመርመር አለበት። ከዚህም ባሻገር ዝናብና ፀሀይ በበቂው መገኘት ለአንድ ሰብል ፍሬ ማፍራትና የፍሬው ሙብዛት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ለአንድ ሰብል ወይም ለተለያዩ ሰብሎች ሙብቀል የአንድ አገር መልክዓምድርና የጠቅላላው አየር ሁኔታ እንደዚሁ ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። ለምሳሌ እንደቡናና ሌሎች የትሮፒካል ፍራፍሬዎች በአውሮፓ ምድር ውስጥ በፍጹም አይበቅሉም። አንድ ሰው ዘሮቹን አምጥቶ አውሮፓ ውስጥ ልሞክራቸው ቢል በፍጹም ፍሬ ሊያፈሩ አይችሉም። ሊያፈሩ የሚችሉት በልዩ እንክብካቤ ከፕላስቲክ በተሰራ በሞቃታማ ቤት(Green House) ውስጥ ብቻ ነው። ይህ ዘዴ ደግሞ ብዙ ምርምርንና ወጪን የሚጠይቅ ስለሆነ ምርትን በብዛት ማምረት በፍጹም አይቻልም።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው ? ወደ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንተረጉመው በአንድ የበለጸገ የካፒታሊስት አገር ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ በሌላ በሁሉም አቅጣጫ ወደ ኋላ በቀረ አገር ውስጥ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የተስተካከለና ጤናማ የሆነ ዕድገት ከማምጣት ይልቅ ተቃራኒውን ነው የሚያስከትለው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለቱም የተለያየ የህብረተሰብ አወቃቀር፣ የአደረጃጀት ልምድና ስልት፣ እንደዚሁም ለየት ያለ የህሊና አወቃቀር ስላላቸው በአንድ የካፒታሊስት አገር ሲሰራበት የነበረውን ፖሊሲ በሌላ አገር ውስጥ በደፈናው ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም።

በሁለተኛ ደረጃ፣ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች የሰውንና የተፈጥሮን ሀብት በስነ-ስርዓትና በተቀላጠፈ መልክ በየመስኮቹ እንዲሰማሩ(allocate) የሚያደርጉና ብቃት ያላቸው ተቋማት የላቸውም። በሶስተኛ ደረጃ፣ በካፒታሊስት የህብረተሰብና የኢኮኖሚ አነነባብ ታሪክ ውስጥ አብዛኛዎቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች እንደዚህ ዐይነቱ የተወሳሰበና በቴክኖሎጂ ምጥቀት የሚገለጽ የዕድገት ደረጃ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ተግባራዊ ያደረጉት ፖሊሲ ተራ የሆነ የገበያ ኢኮኖሚ ወይም የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ሳይሆን፣ ሁለ-ገብ(Holistic) የሆነ የአገር ግንባታ ፖሊሲ ነው ያካሄዱት። በዚህ ዘዴ ነው ቀስ በቀስ ድህነትንና ኋላ-ቀርነትን ሊቀርፉ የቻሉት። ለዚህ ዐይነቱ ሁለ-ገብ የአገር ግንባታ መሰረት ደግሞ የተፈጥሮ ሳይንስ ግኝት ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል። እንዲያውም ፖለቲካ ኢኮኖሚክስ እንደ አገር መገንቢያ ፖሊሲ ከመታወቁ በፊት ሳይንሳዊ ግኝቶች፣ የዕደ-ጥበብ ስራዎችና ከነዚህ ጋር የተያያዘ የንግድ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የከተማዎች መገንባትና የሰዎች ከገጠር ወደ ከተማ ፍሰት ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል።

ይሁንና ግን በተለያዩ የአውሮፓ አገሮች ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተካሄደበት ወቅት አልነበረም። እንደየዕድገት ደረጃቸው የተለያዩ የአውሮፓ መንግስታት በተለያየ የታሪክ ወቅት ውስጥ(Historical Epochs) የተለያዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ አድርገዋል። ከፊዚዮክራቲክስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንስቶ እስከ መርከንታሊዝም ድረስ፣ በገበያ ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ፣ ይሁንና ግን ለካፒታሊዝም ዕድገት የሚያመች የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ ቀጥሎ ደግሞ የኒዎ-ክላሲካልና የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ ከ 1930 ዎቹ ዓመታት፣ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የኬይኔሲያን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግና በመንግስት የሚደገፍ የብድር አሰጣጥ ዘዴ በማስፋፋት ለካፒታሊዝም ምጥቀት አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል።

በየጊዜው የሚታየው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል አሰላለፍ በፖሊሲዎችም ላይ የራሱን ጫና ለማድረግ እንደቻለ ከተደረጉት የርዕዮተ-ዓለም ትግሎች መገንዘብ ይቻላል። የሰራተኛው እንቅስቃሴ ባየለበትና የተገለጸለት ምሁራዊ ኃይል ጎልቶ በወጣበት ዘመን ህብረተሰብአዊ ውዝግብ እንዳይፈጠር መንግስታት ተግባራዊ ለማድረግ የሚገደዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማህበራዊ ባህርይ አለው። በተቃራኒው የካፒታሊስቶች፣ በተለይም የፋይናንስ ካፒታል ኃይል አይሎ በሚወጣበትና ከመንግስት መኪና ጋር በሚቆላለፍበት ጊዜ መንግስታት የሚያወጡትና ተግባራዊ የሚያደርጉት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አብዛኛውን ህዝብ የሚጎዳ ይሆናል። ይህ ዐይነቱ ወደ አንድ ወገን ያደላ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተለይም ከ 1980 ዓ.ም ጀምሮ በአብዛኛዎቹ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በሰፊው ተግባራዊ ለመሆን ችሏል።

ያም ሆነ ይህ በዚህ ዐይነቱ የተወሳሰበና የተሳሰረ የአገር ግንባታ ሂደት ውስጥ መንግስታት በአፍላው ወቅት ከፍተኛውን ሚና

ተጫውተዋል። ኢኮኖሚው እያደገ ሲመጣና የስራ-ክፍፍል ሲዳብር የተከፈተውን ሰፊ ሜዳ በመጠቀም ግለሰቦች የኢኮኖሚ ተዋንያን ለመሆን በቅተዋል። ነገር ግን እነዚህ የተለያዩ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በተለይም በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ሰፋ ያለና ጠለቅ ያለ የጭንቅላት ተሃድሶ ተካሂዷል። በመሆኑም በእየአንዳንዱ የታሪክ ወቅት ተግባራዊ የሆኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሙሉ የረጅም ጊዜ የምሁራዊ ትግልና ክርክር ውጤቶች ናቸው። በማንኛውም የአውሮፓ አገር ውስጥ የተለያየ ግንዛቤና አመለካከት ባላቸው ምሁራን ዘንድ ክርክርና የሃሳብ ልውውጥ ሳይደረግ አንድ ህብረተሰብአዊ ፕሮጀክት በጭፍን ተነድፎ ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም።

ከዚህ ስንነሳ በአውሮፓ ምድር ውስጥ ከ 15 ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ፣ በተለይም የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ጉዳይ ሆኖ መታየት ከጀመረበት ከ 18 ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይዋቀር የነበረው ከህብረ-ብሄርና(Nation-State) ከህብረተሰብ ምስረታ ጋር በመያያዝ ነበር። ሁሉም አገሮች ከተማዎችንና መንደሮችን፣ መንገዶችንና የባቡር ሃዲድ መመላለሻዎችን ከመገንባታቸውና ከመስራታቸው በፊት የገበያ ኢኮኖሚ እያሉ በመጮህና በማስተጋባት በጭፍን የተጓዙበት ጊዜ አልነበረም። ከህብረተሰብ አወቃቀር ጋርና ከህዝብ ደህንነት ጋር የተያያዙ የቤት አሰራሮችና አደጋ መከላከያዎች፣ እንዲሁም ከፍተኛ የተፈጥሮ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ይህንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ማዘጋጀት የኢኮኖሚው አንድ አካል ናቸው።

ይህም ማለት በአውሮፓ የኢኮኖሚ ፖሊስና የህብረተሰብ አገነባብ ታሪክ ውስጥ አንድ ህብረተሰብ ወደ ገበያነት ተቀንሶ የሚታይ ነገር ሳይሆን በተሟላ መልክ በቴክኖሎጂና በማኑፋክቱር፣ እንዲሁም በሳይንስና ሰፋ ባለ በተለያየ የባህል ክንዋኔ የሚገለጽ ነው። በተግባር ሲታይ ተማሪዎች ትምህርት ቤት የሚማሩት የማክሮና የሚክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ቦታ የላቸውም ማለት ነው። በሌላ ወገን ግን ማክሮና ሚክሮ ኢኮኖሚክስ ካፒታሊዝም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን የዳበሩና ለትምህርት የተዘጋጁ መማሪያዎች ናቸው። በመሰረቱ ማክሮና ሚክሮ ኢኮኖሚ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንዴት ከታች ወደ ላይ ቀስ በቀስ እያደገ ሊመጣ እንደቻለና፣ ከአገሮች አልፎ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ሊወስድ እንደቻለ አይነግሩንም፤ ወይም መተንተኛ የቲዎሪ መሳሪያዎች አይደሉም። ይህ ብቻ ሳይሆን ማክሮና ሚክሮ ኢኮኖሚ የካፒታሊስት ኢኮኖሚን ውስጣዊ እንቅስቃሴና የሚመራበትን ህግ አያብራሩም።

- ይህም ማለት በአብዛኛው የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ባለፉት ስድሳ ዓመታት ተግባራዊ የሆኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሙሉ የካፒታሊዝምን ወይም የተሟላ የገበያ ኢኮኖሚን ዕድገት የሚፃረሩ ናቸው። የአፍሪካ አገሮች እንደ ህብረተሰብና ማህበረሰብ ብቃት ያላቸው ተቋማት(Institutions) እንዳይገነቡ መንገዱን የዘጉና የሚዘጉ ናቸው። በዚህም ምክንያት የተነሳ ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት የሚሰማቸውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ልሂቃን ማፍራት አልተቻለም። የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አሳሳችና ሀብት እንዲወድም ወይም ደግሞ የአንድ አገር ሀብት ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲፈስ በማድረግ ቀስ በቀስ ከታች ወደ ላይ የሚያድግ(Organic Growth) የኢኮኖሚ ዕድገትና የህብረተሰብ አወቃቀር እንዳይፈጠር ያደረገና የሚያደርግ ነው። የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ህግና ውስጣዊ-ኃይል የሚፃረር ነው።

- ማለትም ውድድርና ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀቶች የማይታይባቸው፣ ሰፋ ያለ የስራ-ክፍፍል(Division of Labour) የሌለበት፣ ሰፋና ግልጽ የሆነ ገበያ የማይታይበት፤ (Transparent Market Structure) ስለሆነም የአንድ አገር ሀብት የሚባክንበትና በተከታታይ የሰው ልጅ ወደ ድህነት የሚገፈተርበት ነው። በዚህም መልክ በየአገሮች ውስጥ ተግባራዊ የሆኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሙሉ አብዛኛውን ህዝብ ወደ ድህነት ሲገፈትሩ፣ ጥቂቶች ደግሞ ሳይሰሩ የናጠጡ ሀብታም ለመሆን በቅተዋል።

ከዚህ ባሻገር በአፍሪካ አገሮች ውስጥ በተጨባጭ የሚታዩት የኢኮኖሚ ቀውሶች ምክንያትና በካፒታሊዝም ውስጥ አልፎው አልፎው የሚከሰቱት ቀውሶች ምክንያቶቻቸው ይለያያል። በአፍሪካ አገሮች ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ቀውስ በተቋም ቀውስ(Structural Crisis) ሲገለጽ፣ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ አልፎ አልፎ የሚከሰተው ቀውስ ከምርት በብዛት መመረት(Over production) ጋርና፣ የሚመረተው ምርት በቂ ገዢ ካለማግኘት ጋር የሚከሰት ነው። በተጨማሪም አብዛኛው ህዝብ የተመረተውንና ገበያ ላይ ወጥቶ ለሺያጭ የሚቀርበውን የተለያየ ምርት ለመግዛት በማይችልበት(Underconsumption) ጊዜ ፋብሪካዎች የምርት ክንውናቸውን ለማቀዝቀዝ ይገደዳሉ። ይህ በራሱ ደግሞ የሰራተኞችን መባረር ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ ባሻገር ግን ከውጭ ንግድ መቀዝቀዝ ጋር፣ ከጥሬ ሀብት መወደድ ጋር፣ የብድር ወለድ መጨመር፣ እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች

ሲደመሩ፣ ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

- በተጨማሪም ለአየር በአየር ንግድ ሲባል(Speculation) ካፒታል ከተጨባጭ መስኩ (Real Economy) ይልቅ ወደ ፋይናንስ ገበያ ላይ በሚሸሸበት ጊዜ በተጨባጩ ኢኮኖሚ ላይ ሊውል የሚችል የመዋዕለ-ነዋይ እጥረት ሊከሰት ይችላል። በዚህም ምክንያት የተነሳ ውስጣዊ የሆነ ቀውስ(Systemic Crisis) ይፈጠራል። ስለሆነም የስራ-አጥ ቁጥር መጨመር፣ የፋብሪካዎች በምርት ክንውን መቀዝቀዝና፣ የሚመረተው ምርት ገዢ በማጣት ለቀውሱ ጥልቀት ይሰጡታል። ከዚህ ዐይነቱ ውስጣዊ ቀውስ ለመውጣት መንግስታት ተግባራዊ ለማድረግ የሚገደዱት ፖሊሲ በተቅዋም ቀውስ ከሚሰቀየው እንደኛው አገር ካለው ኢኮኖሚ በዐይነት ይለያል። በሌላ ወገን ግን ካፒታሊዝም የዓለምን ገበያ ስለሚቆጣጠር በብዛት የሚመረቱት ምርቶች በዓለም ገበያ ላይ ስለሚራገፉ፣ በዛሬው ወቅት በአንዳንድ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ አልፎ አልፎ የሚከሰተው ቀውስ ከስድሳኛው፣ ከሰባኛውና ከሰማኒያኛው ዓመት ምህረት ይለያል።

በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በግልጽ የሚታዩት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ስር ከሰደደ የተቋም ቀውስ ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህ ዐይነቱ የተቋም ቀውስ በድህነት፣ በቆሻሻ መኖሪያ ቦታዎች፣ በድብቅና ግልጽ በሆነ መልክ የሚገለጽ የስራ-አጥነት፣ በከተማዎች መጨናነቅና በንጹህ ውሃ እጦት የተነሳ ጎልቶ የሚታይ ነው። ለዚህ ዐይነቱ የተቋም ቀውስ ምክንያቶች፣

1ኛ) የውስጥ ገበያው አለመዳበር፣

2ኛ) የተሳሳተ የመዋዕለ-ነዋይ ክንዋኔ ማካሄድና፣ በመጀመሪያ ደረጃ በቅደም ተከተል ተግባራዊ መሆን ያለበትን የመዋዕለ-ነዋይ ክንዋኔ ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባት፣

3ኛ) ከህዝብ ፍላጎት ውጭ የሆነ የመዋዕለ- ነዋይ እንቅስቃሴ ማካሄድ፤ በዚህም ምክንያት የተነሳ ለሚመረቱት ምርቶች በቂ ገዢ (Effective Demand) አለማግኘት፣

4ኛ) በተለያዩ የኢንዱስትሪ መስኮች ዘንድ መተሳሰር አለመኖር፣

5ኛ) በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ ርብርቦሽ አለማድረግ፣ ወይም አንድን ነገር ለመፍጠር መሰረታዊ የምርምር ስራ(Basic Research) አለማካሄድ፣

6ኛ) በኢንዱስትሪዎችና በባንክ መሀከል ግኑኝነት አለመኖር፣

7ኛ) አብዛኛው ህዝብ ብሄራዊ ሀብት ሊፈጥሩ በማይችሉ መስኮች ላይ መሰማራት(Subsistence and Informal Sectors)፣

8ኛ) የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ሲባል በአንድ ወይም በሁለት የጥሬ-ሀብቶች ላይ ብቻ መመካት፤ እነዚህን በፋብሪካ ውስጥ ለፍጆታ በሚያመች መልኩ ሳይለውጡ ወደ ውጭ መላክ፣

9ኛ) በደንብ የታቀዱ የመኖሪያና የመገበያያ ቤቶችና ቦታዎች፣ እንዲሁም ከተማዎችና የመናፈሻ ቦታዎች አለመኖር፣ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው በኢትዮጵያና በተቀሩት የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ጎልተው የሚታዩ የቀውሱ ክስተቶች(Manifestations) ናቸው።

በመሆኑም ለዚህ ዐይነቱ አንድን አገርና ህብረተሰብ የሚገዘግዝና እንደነቀርሳ በሽታ ስር የሰደደ ቀውስ መፍትሄው የኒዎ-ሊበራል የገንዘብ ኢኮኖሚ ፖሊሲ(Monetary economic policy) ተግባራዊ ማድረግ ሳይሆን፣ እነዚህን የተቋም ቀውሶች(Structural Crises) ለመፍታት ሁለ-ገብ የሆነ የኢኮኖሚና የአገር ግንባታ ፖሊሲ ማካሄድ ነው። አንድ አገር እንደ አገርና እንደ ህብረተሰብ ለመኖርና ለተከታታዩ ትውልድ ጠንካራ የኢኮኖሚ መሰረት ሊጥል የሚችለው በዓለም ማህበረሰብ(International Community) የሚቀርበውን የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ሳይሆን ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ከዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ የቫይረስ በሽታ ሲላቀቅ ብቻ ነው።

ከዚህ ዐይነቱ እጅግ አደናጋሪና የተወሳሰበ ሁኔታ ስንነሳ በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተሰራውንና በተደጋጋሚ የሚሰራውን ስህተት እንመልከት። ይህ ዐይነቱ የፖሊሲ ስህተት እንደ ኤይድስ ዐይነት ቫይረስ በመስፋፋት ብዙ አገሮችን፣ አገራችንንም ጨምሮ በቀላሉ መድሃኒት የማይገኝለት በሽታ በመሆን ህብረተሰቦችን እያመነመነና እያመሰቃቀለ ነው። ሁሉም ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበረሰብ፣ በባህል፣ በስነ-ልቦናና በአካባቢ ቀውስ ውስጥ ዘፍቀው በመገኘት መንግስታትና ልሂቃኑ ወዴት እንደሚያመሩ የሚያውቁ አይመስልም። ታዋቂው የአገራችን የአዕምሮና የስነ-ልቦና ተመራማሪና ሃኪም የሆነው ዶ/ር ምህረት ደበበ *„የተቆለፈበት ቁልፍ"* በሚለው መጽሀፉ ውስጥ ቁልጭ አድርጎ እንዳስቀመጠው የአፍሪካ ህዝቦችና አመራሮቻቸው፣ አገራችንንም ጨምሮ *በኦቲዝም* ***(Autism)*** እንዲሰቃዩ ተደርገዋል። በራሳቸው ዓለም ውስጥ

የሚኖሩና የሚያደርጉትን የማያውቁና፣ በህይወታቸውም ዕቅድ የሌላቸው ለመሆን በቅተዋል። በግልጽ የሚታዩ ነገሮችን እንዳያዩ ተደርገዋል።

ጥያቄ እንዳይጠይቁና እንደሰው እንዳያስቡ ታግደዋል። በግልጽ የሚታዩ የተወሳሰቡ ችግሮችን በተራ የአስተሳሰብ ስሌት(Commonsense) ለመፍታት እንዳይችሉ ተደርገዋል። በዚህም ምክንያት የተነሳ ድርጅታዊ አሰራር የጎደለበት፣ ለምንና ለማን፣ እንዴትስ እንደሚሰራ የማይታወቅበት አህጉር በመሆን የሰው ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት እንዲባክኑ ተደርገዋል። በተለይም በኢኮኖሚክስ የሰለጠነውና ፖሊሲ አውጭ የሆነው የአፍሪካ ልሂቅ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በማበርና የጥቅም ተገገር በመሆን አፍሪካን መቀመቅ ውስጥ ከቷታል፤ እየከተታትም ነው። የጥሬ ሀብቷ እንዲዘረፍና ህዝቦቿም መንደሮቻቸውን እየለቀቁ እንዲሰደዱ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ በመነሳት በየዘመኑ የተሰሩትን የፖሊሲ ስህተቶች አጠር አጠር ባለ መልኩ እንመልከት።

**ከ 1950 ዓ.ም ጀምሮ የተሰሩ የፖሊሲ ስህተቶና አሉታዊ ውጤታቸው !**

1ኛ) *የምትክ ፖሊሲ ጉዳይና ውጤቱ* -ለአብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ኢኮኖሚስቶች በ 1950 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በዘመናዊነት ስም(Modernization) በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዐይነት የቱን ያህል ግልጽ እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም። ማለት የሚቻለው ከ 1950 መጀመሪያ ጀምሮ የማኑፋክቸር ተከላ ይካሄድ እንደነበረና፣ ኢኮኖሚውም በቁጥር ሲለካ የተወሰነ ዕድገት እንዳመጣ ይወሳ ወይም ይጻፍ ነበር። ይሁንና ግን ይህ ዐይነቱ የማኑፋክቸር ተከላ ሰፋ ላለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሰረት ሊጥል ይቻል አይቻል፣ ለስራ-ክፍፍል መዳበር ያመች አያመች፣ ለፈጠራ፣ ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዕድገት ያመች አያመች፣ ለከተማዎች መገንባት ያመች አያመች እንደሆን… ወዘተ. በዝርዝር የተጠና ጥናት የለም።

ያም ሆነ ይህ በኢትዮጵያ ምድር ከ 1950 ጀምሮ፣ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ደግሞ ከ 1960 መጀመሪያ ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በምትክ የኢንዱስትሪ ተከላ ላይ ያተኮረ ነው። ይኸውም በዘመናዊነት ስም(Modernization of the American Version) የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በተወሰኑ ወይም በተወሰነ ቦታ በመትከል በተለይም የንዑስ ከበርቴውን የህብረተሰብ ክፍል የፍጆታ አጠቃቀም ማስለመድና „የአሜሪካንን ባህል" ማስፋፋት ነበር። ስለሆነም እንደኮካኮላና ፋንታ፣ ብስኩትና ስኳር፣ እንዲሁም ሲጋራ፣ በመቀጠልም የቢራ ፋብሪካና መጠነኛ የሆነ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ሰፋ ላለና ሁለ-ገብ ለሆነ፣ እንዲሁም ለህብረ-ብሄርና(Nation-State) ለህብረተሰብ ግንባታ የማያመች ወይም መሰረት ሊሆን የማይችል የኢንዱስትሪ ተከላና የፍጆታ አጠቃቀም ነው ተግባራዊ ሊሆን የቻለው።

ይህ ሁኔታ ይበልጥ ለንግድ እንቅስቃሴ፣ በተለይም ወደ ውጭ ለሚወጣና ወደ አገር ውስጥ ደግሞ ለሚገቡ ምርቶችና እቃዎች(Export and Import) አመቺ ሁኔታን ሲፈጥር፣ በዚያው መጠንም በኢንዱስትሪ ተከላና በቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ላይ ሊሰማራ የሚችል የአገር ውስጥ ከበርቴ ብቅ እንዳይልና ተወዳዳሪ እንዳይሆን አግዷል ማለት ይቻላል። ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው በተወሰኑ ነገሮች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከአንድ አካባቢ በማለፍ በአገር ደረጃ የሚስፋፋና እርስ በርሱ በመያያዝ ብሄራዊ ባህርይ ሊይዝ የሚችል አይደለም።

ስለሆነም የስራ መስክ ለሚፈልገው ሊሰራ የሚችል ኃይል በብዛት የስራ ዕድል በመክፈት አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ሊሆን የሚችል አይደለም። ኢንዱስትሪዎችም በመለዋወጫ ዕቃና በጥሬ-ሀብት በውጭ ጥገኛ በመሆናቸው፣ ወደ ውጭ የውጭ ምንዛሪ ካላግባብ ይፈስ ነበር። በዚህም ምክንያት የተነሳና በኢንዱስትሪዎች ውስንነት ወይም ደግሞ ለማደግና ለመስፋፋት አለመቻል የተነሳ ወደ ውስጥ ሰፋ ያለ የውስጥ ገበያ ሊዳብር አልቻለም። በአንፃሩ መስፋፋት የጀመሩት ቡናቤቶች፣ መደነሻ ቦታዎች፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ ሻይቤቶችና ሌሎች ከዕውነተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አንፃር ሲታዩ እዚህ ግባ የማይባሉ „ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔዎች" ናቸው። በዚህም ምክንያት የተነሳ ገንዘብ በሰፊው ለመሽከርከርና እንደ ህብረተሰብአዊ ኃይልም(Social Power) ሆኖ ሊወጣ በፍጹም አልቻለም። ይህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በቁጥር እያደገና ፍላጎቱ እየጨመረ ከመጣው የህዝብ ቁጥር ጋር ለመመጣጠን ባለመቻሉ ማህበራዊና ህብረተሰብአዊ፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ችሏል ። በአገራችንም ለአብዮቱ መፈንዳት የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል።

ይህንን ዐይነቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይዘት በምንመረምርበት ጊዜ ከህዝብ ፍላጎት ጋር ምን ያያዘዋል ? ለአንድ አገርስ ዕድገትና ለህብረተሰብ አወቃቀር ያመቻል ወይ ? በጊዜው እነዚህን የመሳሰሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን አንስቶ የሚከራከር ምሁራዊ ኃይል ነበር ወይ? ወይስ ዝም ብለን ነው የምንነዳው ? በመሰረቱ ከላይ እንዳልኩት በመጀመሪያ ደረጃ የህዝብን መሰረታዊ ፍላጎት ከፍተኛ ቦታ በመስጠት የማይነደፍ ፖሊሲ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አይደለም። በሰፊው የሰራ መስክ ለመክፈትና የስራ-ክፍፍል

እንዲዳብር የማያስችል ፖሊሲ በመሰረቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አይደለም። የሰው ልጅም መሰረታዊ ፍላጎት ኮካኮላ መጠጣትና ሲጋራ ማጨስ አይደለም። የምግብነት ባህርይም የላቸውም። እንዲያውም በአንፃሩ በከፍተኛ ደረጃ ለጤንነት ጠንቅ የሚሆኑና በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ንጥረ-ነገሮችንና ቪታሚኖችን በስነስርዓት በሰውነታችን ውስጥ እንዳይዋሃዱ የሚያደርጉ ናቸው።

ይህ መሆኑ እየታወቀና ከኢኮኖሚ ዕድገት አንፃርም አሉታዊ ውጤቱ እንደሚያመዝን እየታወቀ ለምን ይህ ዐይነቱን ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ተጀመረ ? ከዚህ ስንነሳ በኢትዮጵያ ምድር የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎችና የተስፋፉት የአገልግሎት መስጫ ኩባንያዎች፣ እንደ ባንክና አየር መንገድ የመሳሰሉት በራሳቸው ዓለም የሚኖሩ፣ ትችታዊ አመለካከት ያላቸውና የተገለጸላቸው ኢኮኖሚስቶች የተገለሉ(Enclave) የኢኮኖሚ መስኮች እያሉ የሚጠሯቸውና፣ እርስ በእርሳቸው ያልተያያዙ(Delinked) የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ናቸው። በዚህም ምክንያት የተነሳ ከህዝቡ ጋር ግኑኝነት የሌላቸውና ህብረተሰብአዊ ሀብትም ሊፈጥሩ የሚያስችሉ አይደሉም። በመሆኑም ድሮም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያና የተቀሩት የአፍሪካ አገሮች ብሄራዊ ኢኮኖሚ የላቸውም። ብሄራዊ ኢኮኖሚ የሌለው አገር ደግሞ እንደ አገርና እንደህብረተሰብ የመኖር ኃይል የለውም። የተለያዩ ህብረተሰብአዊ እሴቶችን በማዳበር እርስ በእርሱ ሊተሳሰር አይችልም።

ሰፋ ያለ በሁሉም መልክ የሚገለጽ ምሁራዊ ኃይልም ሊዳበር አይችልም። ይህም ማለት እንደዚህ ዐይነቱ አገር በቀላሉ በውጭ ኃይሎች ይጠቃል፤ ይታለላል። ስለሆነም የአገር ውስጥ የጥሬ-ሀብት በውጭ ኃይሎች በመዘረፍ ሰፊው ህዝብ ወደድህነትና ወደለማኝነት እንዲገፈተር ይደረጋል። ዘለዓለማዊ ድህነትና ጥገኝነት የአንድ አገር መለዮች ይሆናሉ።

2ኛ) *የመሰረታዊ ፍላጎት ፖሊሲና ውጤቱ*- በዘመናዊነት ስም የቋቋሙት የምትክ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ ለመሆን ባለመቻላቸው አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች እንደገና በዓለም ባንክና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በመመከር መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት(Basic Needs Economic Policy) በሚል የኋላ ኋላ ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለ ፖሊሲ በመከተል ወደ ሌላ ቀውስ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል። ፖሊሲው በዕቅድ ደረጃ ትክክል የሆነውን ያህል፣ ተግባራዊ ለመሆን የግዴታ የቴክኖሎጂ መሰረትና ዕውቀት እንዲሁም ገንዘብ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይሁንና እነዚህን በመሳሰሉት ላይ ቅድሚያ ባለመሰጠቱና የመጀመሪያው ዕቅድ ለምን እንደከሸፈ ባለመመርመሩ የመሰረታዊ ፍላጎት ዕቅድ የተጠበቀውን ውጤት አላመጣም። አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ህዝቦች፣ በቂ ምግብ፣ ንጹህ ውሃ፣ መጠለያ ወይም ቤት፣ ህክምናና መሰረታዊ ትምህርት ማግኘት በፍጹም አልቻሉም።

3ኛ) *የአረንጓዴው አብዮትና ውጤቱ*- ከዚያ በኋላ ተግባራዊ የሆነው የአረንጓዴው አብዮት(Green revolution) ተግባራዊ በሆነባቸው አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የተጠበቀውን ውጤት አላመጣም። 1ኛ) ፖሊሲው የየአገሩን ተጨባጭና ባህላዊ ሁኔታዎች ያላካተተ ነው። ይህም ማለት ዕቅዱ ተጠናቅሮ ከውጭ የመጣ ነው። 2ኛ) ዘሮችና ማዳበሪያ እንዳሉ ከውጭ የመጡ ሲሆኑ የየአገሩን የአመጋገብ ባህል ያካተተ አይደለም። 3ኛ) ፖሊሲው አራሹን ገበሬ የጠቀመ ሳይሆን፣ የተጠቀሙት ሀብታም ገበሪዎች ሲሆኑ፣ በአገራችን ደግሞ ራቅ ብለው ይኖሩ የነበሩ የመሬት ከበርቴዎች(Absentee landlord) ነበሩ። ስለሆነም ብድርና ከዚህ ጋር የተያያዙትን ነገሮች ያገኙት እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ናቸው። 4ኛ) ፖሊሲው በጣም ዘመናዊ ከመሆኑ የተነሳ ገበሬውን ከመሬቱ እንዲፈናቀል ያደረገ ሲሆን፣ ዘመናዊ የእርሻ ማሳ ውስጥ ተቀጥሮ መስራት ያልቻለው ወደ ከተማዎች እንዲሰደድና የስራ-አጥ እንዲሆን ያደረገ ነው። ስለሆነም አረንጋዴ አብዮት በመባል የሚታወቀውና የምግብን ዕጥረት ለማስወገድ በሚል 1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው ፖሊሲ እንደተጠበቀውና እንደተነገረለት የአፍሪካን ህዝቦች የምግብ ችግር የፈታ አይደለም።

4ኛ) *የተቋም ማስተካከያ ዕቅድና ውጤቱ*- እነዚህ ፖሊሲዎች በሙሉ የተጠበቀውን ውጤት ባለማምጣታቸው በተለይም በዕዳና በዘይት ዋጋ መናር፣ እንዲሁም በጥሬ-ሀብት ዋጋ መውደቅ የተጎዱት አብዛኛዎች የአፍሪካ አገራት ተግባራዊ ማድረግ የተገደዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተቋም ማስተካከያ ዕቅድ(Structural Adjustment Programm) በመባል የሚታወቀውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ጋና(Ghana)ውስጥ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ተግባራዊ በማድረግ የዕዳ ወጥመድ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል። የንግድ ሚዛናቸው ተዛብቷል። የማምረት ኃይላቸው ተዳክሟል። ከተማዎች ወደ ቆሻሻ መኖሪያነትና መጣያነት ተለውጠዋል። ወደ አገራችንም ስንመጣ የህወሃት አገዛዝ ስልጣን ከጨበጠ ከጥቂት ዐመታት በኋላ እ.አ.አ በ1993 ዓ.ም በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና (IMF) የዓለም ባንክ(World Bank) በመመከርና በመገፋት ተግባራዊ አድርጎታል። ውስጣዊ ይዘቱም፣ የብርን ዋጋ መቀነስ፣(Devaluation) የውጭ ንግዱን ክፍት ማድረግ፣(Liberalization) በዋጋ ላይ የሚደረገውን ገደብ ማንሳትና ገበያው „በጠያቂና በአቅራቢ ህግ" መሰረት

„እንዲገዛ‟ ማድረግ፣ ለልዩ ልዩ የማህበራዊ ፕሮጀክቶች የሚወጣውን ባጀት መቀነስ፣ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የንግድ መደብሮችንና ኢንዱስትሪዎችን ወደ ግል ማዘዋወር፣(Privatization) እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው ተግባራዊ የሆኑትና ጥቂቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀብታም በማድረግ ሰፊውን ህዝብ ደግሞ በማራቆት ወደ ድህነት ዓለም ውስጥ እንዲገፈተር ለማድረግ የበቁት። ይሁንና ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀብታም የሆኑት ግለሰቦችና ድርጅቶች የመፍጠር ችሎታ የሌላቸውና አዲስ ዐይነት የአሰሪዎች ባህል በማዳበር የስራ መስክ ለመክፈት የቻሉ አይደሉም። እነ አቶ መለሰ ዜናዊና የተቀሩት የወያኔ አዛውንቶችና ተከታዮቻቸው ይህን ፖሊሲ *„በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊሲ"* (Developmental State Policy) በማለት ሰፊውን ህዝብ ለማሳመን ሞክረዋል። አብዛኛውም ወያኔን የሚቃወመውና የሚጠላው ኃይል በወያኔ ፖሊሲ ላይ ስምምነት አለው። ስለሆነም በአገራችን ምድር ላይ ለሚታየው የኢኮኖሚ ቀውስ ዋናው ምክንያት በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊስ ነው የሚል ስምምነት አለ። ይህም የሚያረጋግጠው ተቃዋሚው ኃይል በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሆነውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምንነት ለመረዳት እንዳልቻለና፣ የአገራችንን የተወሳሰበ ችግር ለመፍታት የሚያስችል አማራጭ ፖሊሲ ለማቅረበ እንደማይችል ነው።

ስለሆነም ባለፉት 27 ዓመታትና ከዚያም በላይ የተደረገው ትግል ሁሉ ስልጣንን ለመያዝ በመሆኑ ለሳይንስ፣ ለቴክኖሎጂ፣ ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ ጥያቄዎች በፍጹም አትኩሮ አልተሰጣቸውም። ሁሉም የሚመኘውና የሚምለው የአገራችንን የተወሳሰበ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች በንጹህ የገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መፍታት ይቻላል ብሎ ስለሚያምን መሰረታዊ የሆኑ የአገር መገንቢያ መሳሪያዎች ሊረሱ ችለዋል።


ይሁንና ግን የተወሳሰበው የአገራችን ችግር እንዴት በገበያ ኢኮኖሚ አማካይነት ደረጃ በደረጃ እንደሚፈታ የሚነግረን የለም። ድህነትና ረሃብ ተወግድው ህዝባችን ክብር ያለው ኑሮ እንዴት ለመኖር እንደሚችል የሚተነትንና መንገዱን የሚያሳየን የፖለቲካ ፓርቲ ነኝ የሚልና የፖለቲካ እንቅስቃሴ መኖሩን እስካሁን የሰማሁት ነገር የለም። ስለሆነም ከተማዎችና መንደሮች እንዴት እንደሚገነቡ፣ ለሰፊው ህዝብ የሚሆኑ የተለያየ ደረጃና ስፋት ያላቸው የመኖሪያ ቤቶች እንዴትና በምንስ መንገድ እንደሚገነቡ፣ በየቦታው የተለያዩ ህዝብን የሚያሰባስቡና፣ የአገርን የተፈጥሮ-ሀብትና የሰው ኃይልን ለማንቀሳቀስ የሚያስችሉ ተቋማት(Institutions) እንዴት እንደሚገነቡና፣ ሰፊው ህዝብስ እንዴት በስራ ላይ ሊሰማራ ይችላል? በሚሉት መሰረተ-ሃሳቦች ላይ እንደመፍትሄ የሚቀርብ ሃሳብ የለም።


በመሰረታዊ የአገርና የህብረተሰብ ጥያቄዎች ላይ ግልጽነት እስከሌለ ድረስ ስለኢትዮጵያዊነት ብቻ ማውራቱ ይህን ያህልም ትርጉም ሊኖረው አይችልም።

*ምክንያቱም ኢትዮጵያ ልትገለጽ የምትችለው በህዝቦቿ የአኗኗር ስልትና የኑሮ ደረጃቸው ስለሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ የኑሮ ሁኔታና የዕድገት ደረጃቸውን ያላካተተ ኢትዮጵያዊነት ትርጉም አይኖረውም። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያዊነት በሳይንስና በቴክኖሎጂ፣ በጥበብ፣ በአማሩ ከተማዎችና መንደሮች፣ እንዲሁም ከተማዎችና መንደሮች በዘመናዊ የመመላለሻ መንገዶች ሲያያዙ በዚህ መልክ የሚገለጽ ነው።*

የተቋም ማስተካከያ ዕቅድ በኢትዮጵያ ምድር ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት እ.አ.አ ከ 1993 ዓ.ም ጀምሮ በተለይም በንግድ ሚዛኑ ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖና አገራችንን በዕዳ እንደትተበተብ ለማድረግ መብቃቱን በሚከተለው ዲያግራም መመልከቱ ፖሊሲው ያስከተለውን ጠንቅ ለመረዳት ያስችለናል።

የውጭው ንግድ ሚዛን በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር




በእኔ ዕምነት በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮችና ኢትዮጵያንም ጨምሮ ፖሊሲ ነክ በሆኑ ነገሮች ላይ ሳይንሳዊ ክርክርና የቲዎሪ ግምገማና ጥናት አይደረጉም። የተለያዩ አንድን አገርና ህብረተሰብ የሚመለከቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና የአካባቢ ጉዳዮችን ወደ ውጭ አውጥቶ መከራከር የተለመደ አይደለም።

የትምህርት ከሪኩለሞችም ከውጭ የሚመጡና ተግባራዊ የሚሆኑ ስለሆነ ተማሪውን በሁሉም አቅጣጫና ወደ ውስጥ በመመልከት አገር ማለት ምን ማለት ነው? ህብረተሰብስ በምን መሰረት ላይ ቢገነባ የተረጋጋ ሁኔታ ሊፈጠርና ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላለፍ ይችላል? ብሎ እንዲጠይቅ የሚያስችለው አይደለም።

የትምህርት አሰጣጡም የህብረተሰብን ጥያቄዎች ሊፈታ የሚችል ሆኖ ስለማይዘጋጅ ተማሪዎች ትምህርት ጨርሰው በሚወጡበት ጊዜ በግልጽ የሚታዩ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን የመፍታት ችሎታ የላቸውም። ብቃት ያላቸው ተቋማትም ስለሌሉ ትምህርቱን ጨርሶ የሚመረቀው አዳዲስ የሰው ኃይል በስራ በመሰማራትና በየአካባቢው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት በማንቀሳቀስ ህብረተሰብአዊ ሀብት ሊፈጥር አይችልም። ስለሆነም የየአገሩ መንግስታት ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ (International Community) ጋር በማበር የነሱን አገር አፍራሽና ሀብት አውዳሚ ምክር በመቀበል በየአገሮቹ ውስጥ የተዝረከረከ ሁኔታ ሲፈጠር ይህንን የሚቃወምና የሚያጋልጥ የተገለጸለት ምሁራዊ ኃይል ስለሌለ ሰፊው ህዝብ ከፍተኛ በደል ይደርስበታል። ቢኖርም እንኳ ተደማጭነት ስለሌለው፣ ገፍቶ የሄደው አይ ይታሰራል፣ ይገደላል፣ ካሊያም እንዲሰደድ ይደረጋል።

በዚህ መልክ ጠቅላላው ህዝብ የኑሮን ትርጉም እንዳይረዳ ሆኗል፤ ባህልና እሴቶች እንዲፈራርሱ ተደርገዋል። የስራ እሴት ከመስፋፋት ይልቅ ብልግና እንዲስፋፋ መንገዱ ተመቻችቷል። በተለይም የሶስዮሎጂ፣ የፍልስፍናና የስነ-ልቦና ጥናቶች ባልተለመዱበት እንደኛ ባለው አገር ደግሞ ጥቂቶች በመነሳት „ሁሉም አገሮች አንድ ዐይነት የማክሮ ኢኮኖሚ ፓሊሲ ያስፈልጋቸዋል" በማለት የአንድን አገር ውስጣዊ ኃይል ለማዳከም ችለዋል፤ በታትነዋልም።

ከዚህ ስንነሳ ባለፉት ስድሳ ዐመታት በተለያዩ የአፍሪካ አገሮችና በአገራችንም ጭምር ከፍተኛ የታሪክ ወንጀል ተሰርቷል። ኢኮኖሚያዊ ፋሺዝም በመስፋፋት ወደ አንድ ቢሊዮን የሚጠጋ ህዝብ እንዲሰቃይ ተደርጓል። ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ ዛሬም የቀጠለና አህጉሩን እየበታተነ ይገኛል።

በአገራችንና በተቀሩት የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የሰፈነውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ይበልጥ ለመረዳት ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚባለውን ጽንሰ-ሃሳብና መቼና ለምን እንደፈለቀና እንዴትስ ተግባራዊ ለመሆን እንደቻለ ጠጋ ብለን እንመልከት።

በተጨማሪም በተራ የገበያ ኢኮኖሚና በካፒታሊዝም መሀከል ያለውን ልዩነት እንቃኛለን። በእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ላይ ግልጽነት ሲኖር ለአንድ አገር የሚበጅ ሁለ-ገብ የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊስ ለመንደፍ ይቻላል የሚል ዕምነት አለኝ።

ማክሮ ኢኮኖሚ**(Macroeconomy)** ማለት ምን ማለት ነው **?**

ማክሮ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ከግሪክ የመነጨ ሲሆን ትልቅ ወይም ረጅም ማለት ነው። ይህም ማለት ብዙ ነገሮችን ያጣመረ ማለት ነው። ይሁንና ግን ወደዘመኑ የኢኮኖሚ ቲዎሪና ፖሊሲ ስንመጣ ማክሮ ኢኮኖሚ በክስተት ደረጃ የሚታዩ ነገሮችን መግለጫ መሳሪያ እንጂ የካፒታሊስት ኢኮኖሚን ውስጣዊ ህግና እንቅስቃሴ መተንተኛ መሳሪያ አይደለም። ስለሆነም እንደ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት፣(Inflation) የስራ አጥ ሁኔታ፣(Unemployment) የውጭው አጠቃላይ የንግድ እንቅስቃሴ፣(Balance of Payment) አጠቃላዩ የኢኮኖሚ ዕድገት ጉዳይ፣ በተለይም ማደግና መቀዝቀዝ፣ የመንግስት ባጀት ጉዳይ፣...ወዘተ. የማክሮ ኢኮኖሚ „ንፐረ-ሃሳቦች" ናቸው ማለት ይቻላል። ማክሮ ኢኮኖሚ በፖሊሲ ደረጃ በመጀመሪያ ጊዜ በታወቀው የእንግሊዙ ኢኮኖሚስት ኬይንስ በ 1930 ዎች መጀመሪያ ላይ የፈለቀ ነው።

እንደሚታወቀው በ 1920 ዎቹ መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ የካፒታሊስት አገሮች በከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ(Depression) የተመቱበት ጊዜና፣ በብዛት የስራ-አጥ የሚታይበት ዘመን ነበር። በዚህም ምክንያት የተነሳ በአብዛኛዎቹ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ወደ ፖለቲካው ሊዛመት የሚችል ህብረተሰብአዊ ግጭቶች ብቅ ብቅ ያሉበት ጊዜ ነበር።

መንግስታትም ምን ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደሚከተሉ ግራ የተጋቡበት ወቅት ነበር። ቀውሱ እስከተከሰተ ጊዜና ወደ አጠቃላይ ሁኔታ እስከተሸጋገረበት ዘመን አብዛኛዎቹ የካፒታሊስት አገሮች መንግስታት በንጹህ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚመሩና፣ ሁሉንም ነገር ገበያው ይፈታዋል(Laissez Faire) ብለው የሚያምኑ ነበሩ። ይሁንና ግን የቀውሱ ጥልቀት ከፍተኛ በመሆኑና በብዙ መስኮች መዛባት ይታይ ስለነበር ችግሩን ገበያ በራሱ ውስጠ-ኃይል ሊፈታው አልቻለም። በጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በቀውሱ የተጠቃው ጀርመን አገዛዙ ይባስ ብሎ የአንጀት አጥብቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመከተሉ ቀውሱ በመባባስ ለፋሺዝም መነሳት በራሱ አንደኛው ምክንያት ሊሆን በቃ። በሁኔታው የተደናገጠውና ተስፋ የቆረጠው ሰፊ ሰራተኛ ህዝብ ይበልጥ በናዚዎች ጉያ ስር መመሸግን መረጠ።

ይህንን ሁኔታ የተገነዘቡት እንደአሜሪካን የመሳሰሉት አገሮች ፕሬዚደንት ሩዝቤልት በ 1933 ዓ.ም ሲመረጡ በመጀመሪያ ደረጃ በመንግስት የተደገፈ ፖሊሲ ማካሄድ ነው የጀመሩት። ይህ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አዲሱ ስምምነት(The New Deal) በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ያተኮረና የስራ መስክ ለሚፈልገው ሰፊ የስራ-አጥ ኃይል የስራ መስክ የከፈተ ነበር። ፕሮግራሙ ከ 1933-1939 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን፣ የስራ ዕድገትን የሚያስተዳድር ወይም የስራ መስኮችን የሚያዘጋጅ መስሪያ ቤት በማቋቋም ለስራ ቦታ ፈላጊው ቅድመ-ሁኔታዎች ተነጠፉ።

ከዚህም በላይ የኢንዱስትሪዎችን ተከላና ስርጭት የሚያስተዳድር መስሪያ ቤትና ህግ በማውጣት የተቀላጠፈ ስራ መስራት ተቻለ። ወጣቱና በኢንዱስትሪ መስክ ውስጥ ለመሰማራት የማይችለው በዛፍ ተከላና በልዩ ልዩ የመንገድና የቤት ስራዎች ላይ በመሰማራት ሰራ-አጡን ወደ ስራ ዓለም እንዲመለስና ሀብት ፈጣሪ እንዲሆን ተደረገ። ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግና አጠቃላይ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ደግሞ የባንኩን ዘርፍ በአዲስ መልክ ማዋቀር አስፈለገ። ስለሆነም በ 1929/1930 ዓ.ም የታየው ታላቅ የኢኮኖሚ ቀውስ(Depression) እንዳይደገም የአየር በአየር የቁማር ጨዋታ በሚጫወቱ ኢንቬስትሜንት ባንኮችና በንግድ ባንኮች መሀከል(Glass-Steagall Act) ግልጽ የሆነና የማይገናኝ የስራ ክፍፍል ተግባራዊ ተደረገ። በዚህም መሰረት

የንግድ ባንኮች ለተጨባጭ የኢኮኖሚው መስክ፣ ማለትም ለቤት ስራ፣ ለኢንዱስትሪ ተከላና ለሌሎች የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያፋጥኑና እርስ በእርሳቸው ለሚያያዙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ብድር በስርዓትና ግልጽ በሆነ መልክ የሚሰጥበት ሁኔታ ተዘጋጀ። መንግስት ደግሞ በበኩሉ፣ ሰፋ ባለ የቤት ስራ፣ የመንገድና የድልድዮች ስራ፣ እንዲሁም አዳዲስ የባቡር ሃዲዶችን መስራትና ያለውንም መጠገን፣ እንደቴኒሲ ሸለቆ በመሳሰሉት ትላልቅ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ላይ በመሰማራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለብዙ ሚሊዮን ህዝብ የስራ መስክ ሲከፍት፣ በዚያው መጠንም ኢኮኖሚው እያደገ መጣ። ይህ ዐይነቱ በመንግስት የተደገፈ ሰፋ ያለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የንጹህ ገበያን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስህተትነቱን በማሳየት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዓምር ሊፈጠር ቻለ። ኢኮኖሚስቱ ኬይንስ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በውስጡ ተፈጥሮአዊ መዛባት ስላለውና ራሱን በራሱ በማንቀሳቀስ ከቀውስ ለመውጣት ስለማይችል የግዴታ የመንግስት ጣልቃ-ገብነት እንደሚያስፈልገው በማመልከትና በማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴም በምን መልክ በገንዘብ እንደሚደጎም ወይም ፋይናንስ እንደሚሆን አሳየ።

በሱም ዕምነት መንግስት የግዴታ ከባንክ በመበደር ኢኮኖሚውን ማንቀሳቀስ አለበት። ማርክስ በ19ኛው ክፍለ-ዘመን እንዳረጋገጠውና ኬይንስም ተመራምሮ እንደደረሰበት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በዕድገትና በቀውስ የሚገለጽ ስርዓት እንደመሆኑ መጠን ቀውሱን የሚያስወግድና ወደ ሚዛናዊነት ሁኔታ ሊያመጣ የሚያስችለው ውስጣዊ መሳሪያ ወይም ህግ የለውም። ስለሆነም ቀውሱ ስር ከሰደደ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ማህበራዊ መናጋትን ስለሚያስከትል የግዴታ መንግስት ጣልቃ በመግባት ኢንዱስትሪዎች በድሮ የማምረት ኃይላቸው እንዲያመርቱና የስራ መስክም እንዲከፍቱ አስፈላጊ የሆኑ የመዋዕለ-ነዋይ ድጎማዎችን ማድረግ አለበት።

በዚህ መልክ ብቻ በገንዘብና በተጨባጭ ኢኮኖሚው መስክ ያለውን ግኑኝነት ማጠንከር ሲቻል፣ መንግስትም ከቀረጥ ገቢ ስለሚያገኝ የተበደረውን ገንዘብ መክፈል ይችላል፤ የተቀረውን ደግሞ በልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ላይ በማዋል ለኢኮኖሚው ዕድገት ልዩ ዕምርታን ይሰጠዋል።

ይህ ኬይንስ ያዳበረው የኢኮኖሚ ቲዎሪና ፖሊሲ ይበልጥ ተግባራዊ የሆነው ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ነው። በጦርነቱ የተጎዱ አብዛኛዎቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች፣ በተለይም እንደጀርመን የመሳሰሉት በመጠኑም ቢሆን በማርሻል ፕላን በመደገፍ፣ የተንኮታከተውን ኢኮኖሚያቸውን አስራ አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደገና መልሰው ሊገነቡ ችለዋል። እዚህ ላይ ወሳኙ፣ የማርሻል ፕላን ሳይሆን፣ ውስጣዊ ፍላጎት መኖር፣ የአደረጃጀት ስልትና አገርን ለመገንባት ቆርጦ መነሳት ዋናው የኢኮኖሚው ዕድገትና የአገር ግንባታ መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው።

በመሆኑም ለትናንሽና ለማዕከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣ እንዲሁም ለሰፊው ህዝብ ቤቶችን ለመስራት ፋይናንስ የሚያደርግ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለ ልዩ ዐይነት የብድር ባንክ(Credit Bank) በማቋቋምና፣ የቁጠባ ባንኮችን በማስፋፋት ኢኮኖሚውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሳደግ ችለዋል። በሰፊው የስራ መስክም በመክፈት በአጭር ጊዜ ውስጥ በቴክኖሎጂ ለመመንጠቅ ችለዋል። በተለይም የተለያዩ የቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኮሌጆችንና የምርምር ጣቢያዎችን፣ እንዲሁም የተግባረ-ዕድ ማሰልጠኛ ማዕከሎችን በማቋቋምና በተለያዩ ክፍለ-ሃገራት በእኩል ደረጃ እንዲሰራጩ በማድረግ አፋጣኝ የሆነ ዕድገትን ማምጣት ችለዋል።

በዚህም መሰረት ልዩ ልዩ ምርቶችን በማምረት የህዝቦቻቸውን ፍላጎቶች ማርካት ችለዋል። በቅድሚያ ግን ተግባራዊ ማድረግ የጀመሩት፣ የመኖሪያ ቤቶችን ችግር ወይም ጥያቄ መፍታት፣ የንጹህ ውሃን ጉዳይ ማስተካከልና በየቤቱ እንዲገባ ማድረግ፣ የምግብና የመብራት እንዲሁም የማሞቂያና የምግብ ማብሰያ ችግሮችን መፍታት የኢኮኖሚው መሰረተ-ሃሳቦችና ቅድሚያም የተሰጣቸው ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች ሳይፈቱና ሳይሟሉ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት አይቻልምና።

ስለሆነም በአጠቃላይ ሲታይ በአውሮፓ ምድር ውስጥ ቀድሞም ሆነ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ህብረተሰብንና አገርን በጠንካራ መሰረት ላይ ከመገንባት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴም በተራ ንግድ ወይም በችርቻሮ የሚገለጽ ሳይሆን፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እንዲሁም በጠራ ስራና ድርጅታዊ አዘገጃጀት ብቻ ነው።

ከዚህም ባሻገር በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ሰፋ ያለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የጥበብንና የልዩ ልዩ ባህሎችን ዕድገትና መዳበርን ያግዛል። እንደ ጥንታዊ የሙዚቃ ዐይነቶች፣ ድራማዎችና የፖለቲካ ቀልዶች፣ ሙዚየሞችና ስዕሎች እንዲሁም ልዩ ልዩ የስፖርት ዐይነቶች በተወሰነ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃ የመስፋፋት ዕድል ይኖራቸዋል።

በዚህ ዐይነቱ የባህል እንቅስቃሴ ሰፊው ህዝብም የበለጠ የመተሳሰርና ራሱን በራሱ የማግኘት ዕድል ያጋጥመዋል። ሰው መሆኑን በመረዳት የበለጠ ፈጣሪ ለመሆን ይችላል። በዚህ መልክ ስለኢኮኖሚ ዕድገትና ስለአገር ወይም ስለህብረተሰብ ማውራት ይቻላል። ኢኮኖሚያዊ መሰረታቸው ጠባብ የሆነና ህዝቡም ተዝረክርኮ የሚኖርባቸው አገሮች እንደህብረተሰብና እንደማህበረሰብ ወይም እንደ አገር ሊቆጠሩ በፍጹም አይችሉም።

እንደገና ወደ ማክሮ ኢኮኖሚ ጽንሰ-ሃሳብ እንምጣ። ይህንን በንፅፅር (Analaogy) እንመልከተው። ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ማክሮ ማለት ትልቅ ነገር ማለት ነው። እንደሚታወቀው ማንኛውም ግዙፍ ወይም ትልቅ ነገር የትናንሽ ንጥረ-ነገሮች ክምችት ነው። ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው ነገሮች በሙሉ የመጨረሻ መጨረሻ የልዩ ልዩ አካሎችና ንጥረ ነገሮች ድምሮች ናቸው። ለምሳሌ ማንኛውንም ሰው እንደማክሮ ልንወስደው እንችላለን።

እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ሁሉ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች፣ የነርቭ ሲስተምና በሌሎች የሚገለጽ ነው። ሰውን ሰው የሚያደርገው እንዲንቀሳቀስ፣ እንዲያስብና እንዲሰራ፣ እንዲሁም አካባቢውን ወይም ተፈጥሮን እንዲለውጥ የሚያስችሉት ልዩ ልዩ የሰውነት አካሎች ስላሉት ነው። እነዚህ ልዩ ልዩ ነገሮችን እንደሚክሮ ልንወስዳቸው እንችላለን። ይህም ማለት በተለያዩ የሰውነት አካሎች መሀከል ባለው የስራ-ክፍፍልና ቅንብር ሰውነታችን መንቀሳቀስና ማሰብ ይችላል።

ይህንን ወደ ኢኮኖሚ ስንመነዝረውና ወደ ማክሮ ኢኮኖሚ ከመምጣታችን በፊት እዚህና እዚያ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ትናንሽና ማዕከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴዎች መኖር አለባቸው። በእነዚህ እዚህና እዚያ ተሰበጣጥረው በሚገኙ፣ ይሁንና ደግሞ በገንዘብ አማካይነት የሚገናኙና፣ ከፍጆታ ዕቃዎች ባሻገር ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የሚሆኑ ልዩ ልዩ የመለዋወጫ ዕቃዎችንና መሳሪያዎችን በሚያመርቱት መሀከል መተሳሰር ሲኖር ማክሮ ብለን የምንጠራው ትልቁ ነገር ይፈጠራል። የካፒታሊዝምን ዕድገት ስንመለከት ትናንሽና የማዕከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣ እንዲሁም የዕደ-ጥበብ ክንውኖች ከመፈጠራቸው በፊት ማክሮ ብለን የምንጠራው ትልቁ ነገር አልተፈጠረም።

ስነስርዓት ያላቸው ከተማዎችና መንደሮች ሳይገነቡና በዕቅድ የሚካሄድ የንግድ እንቅስቃሴ ከመዳበሩ በፊት ስለማክሮ ኢኮኖሚ ማውራትም በፍጹም አይቻልም። ይህንን ዐይነቱን ከትንሽ ነገር ተነስቶ ከሌላው ጋር በመያያዝና ወደግዙፍነት የመለወጥን ሁኔታ በተፈጥሮ ውስጥ የምንመለከተው የዕድገት ሂደት ነው። እንደየሁኔታው በተለይም ህይወት ያለው ነገር፣ ራሳችንም ሰዎች ከትንሽ ነገር ተነስተን ነው እያደግንና የሰውነት አካሎቻችን ሁሉ ቅርጽና መልክ እየያዙ ሊመጡ የሚችሉት። በተለይም ደግሞ ልዩ ዐይነት ጥንቃቄ የተሞላበት እንክብካቤ ከተደረገ፣ አትክልቶች ጥሩ ፍሬ ሊሰጡ ይችላሉ፤ የሰው ልጅ ደግሞ በአካሉ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም በመዳበር የማገናዘብ፣ የማወዳደር፣ ጠለቅ ብሎ የማሰብና የመመራመር፣ እንዲሁም አርቆ-የማሰብ ኃይሉ እያደገ ይመጣል።

ከዚህ ስንነሳ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች በአመንክዮ(Logically) ሳያስቡ በዓለም አቀፍ ተቋማትና (International Insitituions) „በአማካሪ" ኩባንያዎች(Consulting Companies) እየተመከሩ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ፖሊሲዎች በሙሉ መቀመቅ ውስጥ የከተቷቸውና የሚከቷቸው ናቸው።

ይህንን ከላይ ለማሳየት የሞከርኩትን ከትንሽ ነገር ተነስቶ ወደ ትልቅ ነገር ማደግና፣ በሌላ ወገን ደግሞ አንድ ትልቅ ነገር የተለያዩ ክፍሎች ጥምር መሆኑን ካለመረዳት የተነሳ ተግባራዊ የሚሆኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሙሉ ከፍተኛ ህብረተሰብአዊ ውዝግብን እየፈጠሩና ለአካባቢ ቀውስ ምክንያት እየሆኑ ነው። የጥሬ-ሀብት በተቆጠበና ስነ-ስርዓት ባለው መልክ ተቆፍሮ በመውጣትና በፋብሪካ ውስጥ በመፈበረክ ለአንድ ህዝብ የሚጠቅም ህብረተሰብአዊና ብሄራዊ ሀብት(National Wealth) እንዳይፈጠር እየተደረገ ነው። ሌላው አደናጋሪው ነገር ካፒታሊዝም በፍጥነት ዓለም አቀፋዊ ባህርይ መውሰድ ከጀመረ ጀምሮ ተፈጥሮአዊ የሆነውን የሰውን ልጅና የህብረተሰብ ዕድገት እንዲዛነፍ ወይም እንዲሳሳት በማድረጉ እንደኛ የመሳሰሉ በተለይም በምሁር ደረጃ ያልዳበሩ አገሮች የማያስፈልግ የኢንዱስትሪ ተከላ በማካሄድ አጠቃላዩን የህብረተሰብ ዕድገት እንዲረበሽና ምስቅልቅሉ እንዲወጣ ለማድረግ በቅተዋል።

በተፈጥሮና በሰው ልጅ መሀከል ያለው ጤናማ ግኑኝነት እንዲረበሽ በማድረግ ከተማዎች ወደ ምድረበዳነት ተለውጠዋል። ከተማዎች ከህንፃዎችና ከመንገዶች በስተቀር ዛፎችና ወንዞች የሌሉባቸው በመሆን የሰው ልጅ አኗኗር ስልትና ባህርይ ሊናጉ ችለዋል። ከመጀመሪያውኑ መቅደም ከሚኖርበት ነገር ላይ ከመነሳት ወይንም እዚያ ላይ ከመረባረብ ይልቅ የማይሆን ነገር ላይ በመሰማራት የሰውን የማሰብ ኃይል ለማቃወስ ችለዋል፤ የተፈጥሮ ሀብትም በከፍተኛ ደረጃ እንዲባክን አድርገዋል።

በሌላ አነጋገር፣ የምግብን፣ የቤትን፣ የንጹህ ውሃን፣ የህክምናን፣ የትምህርትንና የከተማ ግንባታዎችን ከማስቀደም ይልቅ የሸንኮራ አገዳ በመትከል ወደ ስኳር ምርት ያመራሉ። ከንጹህ ውሃ ይልቅ የኮካኮላ ኢንዱስትሪ ይከፍታሉ። እህል ከማብቀል ይልቅ ትምባሆና አበባ ተከላን ያስቀድማሉ። በዚህ መልክ ተፈጥሮአዊ የሆነውን የሰው ልጅ ፍላጎትና የህብረተሰብ ዕድገት ይጨናገፋሉ። ስለሆነም በየአንዳንዱ የታሪክ ወቅት ስህተት እየተሰራ አንድ ህብረተሰብና አገር በችግር ላይ ችግር እየተደረበባቸው የማይወጡት ማጥ ውስጥ እንዲወድቁ ተደርገዋል።

በአገራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለሚወራው ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር ስንመጣ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች እጅግ በተዛነፈ መልክ ያስፋፉትን የገንዘብ የአንጀት አጥብቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲ(Austerity or Monetary policy) በመውሰድ ነው ሁሉም አገር የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስፈልገዋል እየተባለ የሚናፈሰውና እንደዳዊት የሚደገመው።

ስለሆነም በዚህ ዐይነቱ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሰረት ሁሉ ነገር ለገበያ መተው አለበት። መንግስት በምንም ዐይነት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ኢንዱስትሪዎችና የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች፣ ውሃ፣ መብራት፣ የባቡር ሃዲድ፣ ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች ሁሉ ወደ ግል መዛዋወር ወይም መሸጥ አለባቸው። የመንግስት ተግባር ዝም ብሎ እጁን አጣጥፎ ከመቀመጥ በስተቀር በኢኮኖሚውና ሌሎች ማህበረሰቡን በሚመለከቱ ነገሮች ውስጥ ጣልቃ በመግባት የገበያን ህግ የሚፃረሩ እርምጃዎች መውሰድ የለበትም ።

ይህ ዐይነቱ የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ እ.አ ከ 1979 ዓ.ም ጀምሮ በብዙ አገሮች ውስጥ ተግባራዊ በመሆን፣ እንደ እንግሊዝ በመሳሰሉት ጥንታዊ የኢንዱስትሪ አገሮች ውስጥ የኢንዱስትሪዎችን መፈራረስ(Deindustrialization) አስከትሏል። የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ከተጨባጩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ(Real Economy) ወደ አየር በአየር ንግድ (Financial

Market) ላይ እንዲያዘነብል በማድረግና፣ የማዕከላዊ ባንኮች በሚከተሉት የአልቦ ወለድ የብድር አሰጣጥ ፖሊሲ (Zero Interset Rate) አማካይነት ጥቂት ባለሀብቶች የባሰውኑ እንዲናጥጡ በማድረግ፣ እንደወል ስትሪት (Wall Street) የመሳሰሉት ደግሞ እንደዋና የኢኮኖሚ ዘርፍ ሆነው በመታየት ከፍተኛ የሀብት ማውደም የሚካሄድባቸው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለመሆን በቅተዋል።

በዚህ መልክ ይህ ዐይነቱ የብድር አሰጣጥ ፖሊሲና የአየር በአየር ጨዋታ በከተማዎች ውስጥ የኑሮ ሁኔታ እንዲወደድ ሲያደርግ፣ በተለይም እንደለንደንና ፓሪስ እንዲሁም ኒዎርክ የመሳሰሉት ከተማዎች ውስጥ ሰው መኖር የማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። ቤቶችና መሬት ወደ አየር በአየር ንግድነት በመለወጥ(Speculation Objects) ከፍተኛ የሆነ የሀብት ሽግሽግ ይካሄዳል።

በዚህ ላይ ከተለያዩ አገሮች ባለሀብቶች፣ ከራሺያ፣ ከዩክሬይን፣ ከቻይናና ከተለያዩ የአረብ አገሮች በመምጣትና ቤቶችን በመግዛትና በመሸጥ ተራው ሰው ቤት ተከራይቶ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ተደርጓል።

በዛሬው ወቅት ማንኛውም ተራ ሰው የራሱን የግል ቤት የመስራት ኃይል ወይም አቅም የለውም። አሜሪካም ይህንን መንገድ በመከተሉ እንደዚሁ ሰፋ ያለ የኢንዱስትሪ መፈረካከስ ሲደርስበት፣ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ኢንዱስትሪዎችን በመንቀል ሜክሲኮና ቻይና በመውሰድ ለእነዚህ አገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተወሰነ አስተዋፅዖ ማድረግ ችለዋል። በአንፃሩ በእነዚህ አገሮች ውስጥ በርካሽ የሰው ጉልበት የሚመረቱት ምርቶች በአሜሪካን ገበያ ላይ በመሸጥ ገበያውን አጥለቅልቀውታል። በዚህም ምክንያት የአሜሪካን የውስጥ ገበያና የውጭው ንግድ በከፍተኛ ደረጃ በመዳከሙ ከካፒታል ገበያ፣ በተለይም ከቻይና ገንዘብ እንዲበደር ተገዷል።

የአገራቸውን ተጨባጭ ሁኔታና የሰውን ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ማንበብ የማይችሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ርዕዮተ-ዓለም አራማጆች ማንኛውም አገር የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ(Macroeconomy Policy) ያስፈልገዋል እያሉ አገራችንን የዓለም የገንዘብ ድርጅት(IMF)፣ የዓለም ባንክና፣ እንዲሁም የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ „*አማካሪዎች*"**(**Consulting Companies) መጫወቻ ለማድረግ በቅተዋል።

እንደምናየውና የኢትዮጵያ ህዝብ የኑሮ ሁኔታ እንደሚያረጋግጥልን እነዚህ ዓለም አቀፉዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተዋንያንና የአገራችን የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ቀስቃሾች የህዝባችንን መሰረታዊ ችግሮች መፍታት አልቻሉም። እንዲያውም ህዝባችን የባሰውኑ ደሃ እንዲሆን በማድረግ ጤናማ ኑሮ እንዳይኖር አድርገውታል። የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ከሆነ ከ 1993 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባችን ብቻ ቁጥራቸው የማይታወቅ የቆሻሻ መኖሪያ ቦታዎች(Slums) ተስፋፍተዋል።

በሌላ ወገን ደግሞ በመንግስት የሚደገፉና ከባንክ በርካሽ ወለድ ብድር የሚያገኙ በተለይም ከአንድ ብሄር-ሰብ የተውጣጡ ግለሰቦች ደሃውን ኗሪ ሰው ከመሬቱ በማፈናቀል ፎቅ ቤቶች በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ የናጠጡ ሀብታሞች ሊሆኑ በቅተዋል። በዚህ መልክ የአገራችን ሀብት እንዲዘረፍና ከፍተኛ የሆነ የአካባቢ ቀውስ እንዲከሰት አድርገዋል። ይህ ዐይነቱ የህብረተሰብንና የተፈጥሮን ህግ፣ እንዲሁም የሰውን ምንነት በሚገባ የማያገናዝብ ኢ-ሳይንሳዊ የሆነና የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በመሆኑ መጠነ-ሰፊ የሆነ፣ በቀላሉ መፍትሄ ሊገኝለት የማይችል የኢኮኖሚና የማህበራዊ ቀውስ በአገራችን ምድር ሊከሰት በቅቷል። ማንም ኃይል በቀላሉ ሊፈታው እንዳይችል ተደርጓል።

ነገር ግን ከፍተኛ የአስተሳሰብ ለውጥ ከተደረገና የአሰራር ስልትም ከተቀየረ አፍጠው አግጠው የሚታዩ ችግሮችን በጋራ መቅረፍ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ዋናው መሰረተ-ሃሳብ በራስ መተማመን ነው።

ከዚህ ችግር ለመውጣት መሰረታዊ ሃሳቦችን እንረዳ። ይህም በተራ ገበያና በካፒታሊዝም መሀከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ያስፈልጋል። በእኔ ዕምነት አብዛኛዎቹ ስለማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አስፈላጊነት የሚወተውቱ ኢኮኖሚስቶች የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ምን እንደሆነና በምንስ ዐይነት ህግ እንደሚመራ የሚያውቁ አይመስለኝም። የዚህ ክፍተት ዋናው ችግር አብዛኛዎቹ ኢኮኖሚስቶች የኢኮኖሚ አስተሳሰብን ታሪክና የካፒታሊስት ኢኮኖሚን ዕድገት ደረጃ በደረጃ እንዴት እንደተገነባ ባለመማራቸው ነው።

ሁሉም የሚማሩት ሳሙኤልሰን ያስፋፋውን የኢኮኖሚ ትምህርት ስለሆነና በኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች እጅግ በተሳሳተ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበውን እንዲማሩ በመደረጋቸው የካፒታሊዝምን ኢኮኖሚ መሰረተ-ሃሳብና ውስጣዊ ህግ እንዳያውቁ ሆነዋል። ስለሆነም ከአገር ገንቢነት ይልቅ አገርን አፍራሽና ሀብትን ቸብቻቢ ለመሆን ችለዋል። የሚያወሩትም ፕላቶ እንደሚለንና እንደሚያስተምረን *„እንዴት ኢድርገን እንደማህበረሰብና እንደህብረተሰብ እንኑር፣ አገርን በጸና መሰረት ላይ እንገንባ"* ሳይሆን *እንደተራ ነገር ነው የሚያስቡት።* ይህም ማለት አንድ አገር ወደ ተራ ገበያነት እንዲቀነስና የሰው ልጅም ባከና እንዲቀር የሚያደርግ አስተሳሰብ ነው በአገራችን ምድርና በተቀሩት የአፍሪካ አገሮች በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋትና የሰውንም ጭንቅላት መያዝ የቻለው። ይህ ዐይነቱ የተበላሸ አስተሳሰብ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ በመውሰድና ሁሉም አገሮች ተግባራዊ በማድረጋቸው ለሙስናና ለተዛባ የሀብት ክፍፍል ዋና ምክንያት በመሆን፣ ወደ ውስጥ ደግሞ በተስተካከለ የማኑፋክቸር ተከላ ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪ ግንባታ እንዳይካሄድ በማገድ የውስጥ ገበያ እንዳያድግ ተደርጓል። አሁን በቅርቡ በፕሮፌሰር ስቴፋን ሹልማይስተር(Stephan Schulmeister) የታወቁት የአውስትሪያ ኢኮኖሚስት ታትሞ በወጣው መጽሀፍ፣ ***„The Road to Prosperity"*** በሚለው መጽሀፋቸው ውስጥ ይህ ዐይነቱ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን በአገሮች ውስጥ እንዴት የሀብት ክፍፍል መዛባት እንደፈጠረና፣ በዚያው መጠንም ስርዓቱን የሚቀናቀኑ የፋሺሽትና ዘረኛ ድርጅቶች ብቅ ማለት እንደቻሉ ያመለክታል። በፕሮፌሰሩ ዕምነትና በኢኮኖሚክስ ቲዎሪና በተፈጥሮ ሳይንስ ምርምርም እንደታየውና እንደተረጋገጠው በታሪክ ውስጥ ዘለዓለማዊነት ያለውና ሊኖረው የሚችል አንድ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የለም። አዳዲስ የህብረተሰብ ግኑኝነቶችና የሚከሰቱ ችግሮች አዳዲስ ቲዎሪና ፖሊሲዎችን የሚሹ ስለሆነ፣ በተለይም የሳይንስን መንገድ እከተላለሁ የሚል የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲን እንደቀኖና መውሰድና ካለሱ አማራጭ የለም እያለ መስበክ የለበትም።

በፕሮፌሰር ሹልማይስተር ዕምነት በኒዎ-ሊበራሊዝም ላይ የተመሰረተው የማክሮ ኢኮኖሚ ቲዎሪና ፖሊሲ ፀረ-ኢንላይተሜንት ነው። ይህም ማለት በአውሮፓ ምድር ውስጥ ከስድስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እስከ አስራአምስተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የአውሮፓን ህዝብ ጭንቅላት ቆልፎ እንደያዘውና የሳይንስንና የቴክኖሎጂን ዕድገት አጥብቆ እንደተዋጋው የካቶሊክ ሃይማኖት ቀኖናዊ አስተሳሰብ የዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፀረ-ስልጣኔ ነው። በፕሮፌሰር ሹልማይስተር ዕምነት በኒዎ-ሊበራሊዝም ላይ የተመሰረተው ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ሳይንስ ሳይሆን ርዕዮተ-ዓለም ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይንስንና የቴክኖሎጂን ዕድገት መስፋፋትና የብዙ ቢሊዮን ህዝቦችን ህይወት ማቃለል አጥብቆ የሚቃወም ነው። ድህነትንና ቆሻሻ የመኖሪያ ቦታዎችን በማስፋፋት በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች አቅመ-ቢስ ሆነው እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው። መብታቸውን እንዳያውቁና ለመብታቸውም እንዳይከራከሩና እንዳይታገሉ ሁኔታዎችን ውስብስብ የሚያደርግ ነው። የፖለቲካና የኢኮኖሚ ልሂቁን እንዲሳሳት በማድረግ ድህነት እንዲስፋፋ የሚያደርግና ህብረተሰብአዊ ውዝግብ እንዲፈጠር የሚያስገድድ ነው።

ከዚህ ስንነሳ በተፈጥሮ ሳይንስ አስተሳሰብ ውስጥም በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ሳይንቲስቶች ከቀደመው ለየት ያለ ሳይንሳዊ

ምርምርና መንገድ በማሳየት ለሳይንስ ምጥቀት አመቺ ሁኔታን እንደፈጠሩ አመልክተዋል።

በመሆኑም የዛሬው የኒዎ-ሊበራል ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ሊኖረውና ዘለዓለማዊም ሊሆን በፍጹም አይችልም። እያንዳንዱ መንግስትና ማህበረሰብ ለራሱ ዕድገትና ለህብረተሰብ መተሳሰር የሚያመች የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማውጣቱ ጉዳይ የራሱ መብትና ኃላፊነት ብቻ መሆን አለበት። ማንም የውጭ ኃይል እየመጣ ይህንን አድርግ እያለ አንድን አገር የማተረማመስና ህብረተሰብአዊ ሰላምን የማደፍረስ መብት የለውም። ምክንያቱም በአንድ አገር ውስጥ ታሪክ ሊሰራና ተከታታይነትም ሊኖረው የሚችለው በአንድ መንግስት ንቃተ-ህሊናና በአንድ ህዝብ ቆራጥ ተሳትፎ ስለሆነ ነው። ይህንን መሰረታዊ ሃሳብ ከተመለከትን በኋላ በገበያ ኢኮኖሚና በካፒታሊስት ኢኮኖሚ መሀከል ያለውን ልዩነት ደግሞ እንመልከት።

በተራ ገበያ ኢኮኖሚና በካፒታሊዝም መሀከል ያለው ልዩነት **!!**

የገበያ ኢኮኖሚ መቼና የት ቦታ እንደተጀመረ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ባይሆኖርም እንደሜሶፖታሚያ በመሳሰሉት በጊዜው ሻል ያለ መንግስታዊ አወቃቀርና ህገ-መንግስት ባላቸው አገዛዞች የገበያ ኢኮኖሚ እንደዳበረ የኢኮኖሚ ታሪክ መጽሀፎች ያረጋግጣሉ። በታሪክ ውስጥ ዛሬ የምናውቀውና የምናየው ገበያ ዐይነት ወይም የገበያ ኢኮኖሚ ከመፈጠሩ በፊት አብዛኛዎች ማህበረሰቦች የሚያመርቱን ምርት የሚለዋወጡበት መድረክ ነበራቸው። በጥንት ዘመን ይህ ዐይነቱ ገበያ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች ተግባሮችም ነበሩት። ሃሳብ ለሃሳብ የሚለዋወጡበትና ገገርዎችም አዋጅ የሚያስነግሩበትና ፍርድም የሚሰጡበት መድረክ ነበር። በዕቃ ልውውጥና በገንዘብ ዕድገት የተነሳ ገበያ ከጥንታዊ ባህርይው በመላቀቅ ምርት ብቻ የሚሸጥበት መድረክ ሆነ።

በአንድ አካባቢ ተሰበጣጥረው ይኖሩ የነበሩ ሰዎችና ከሌላ ቦታ እየመጡ ምርትንም ሆነ እንደጨው የመሳሰሉትን በመለዋወጥም ሆነ በመሸጥ ለገበያ ኢኮኖሚ የመጀመሪያውን መሰረት እንደጣሉ ታሪክ ያረጋግጣል። የስራ-ክፍፍል ሲዳብርና አንዳንድ ግለሰቦችም በጀመሩት ሙያ እየገፉ ሲመጡና፣ ያመረቱትንም ምርት ገበያ ላይ አውጥተው ሲሸጡና የተሻለ ጥቅምም ሲያገኙ ምርትን በገንዘብ መለወጥ ለገበያ መዳበርና መስፋፋት አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ችሏል።

በተለይም የሩቅ ንግድ(Far Trade) ገፊ ኃይል(Catalyst) በመሆን ለገበያ ኢኮኖሚ በዐይነትም ሆነ በብዛት መስፋፋት ዕምርታን ሰጥቶታል። ይሁንና ግን የንግድ ልውውጥ እንዲካሄድ ደግሞ የሁሉም መለኪያ የሚሆን ነገር ስላስፈለገ የግዴታ ገንዘብ ለሚለው መሰረተ-ሃሳብ መንገድ ከፈተ። ባጭሩ አብዛኛዎቹ የዓለም ማህበረሰቦች ወደዛሬው ዐይነቱ የገበያ ኢኮኖሚ ከመሸጋገራቸው በፊት ብዙ ውጣ ውረዶችን እንዳለፉ ታሪክ ያረጋግጣል። የገበያ ኢኮኖሚ አፍላቂዎች ወይም ፈጣሪዎች የዛሬዎቹ የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት አገሮችና አሜሪካ እንዳይደሉ የታወቀ ነገር ነው። የገበያ ኢኮኖሚ እዚህና እዚያ መታየቱና ቀስ በቀስም ዓለም አቀፋዊ ባህርይ መውሰዱ ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ ሳይታሰብ የተፈጠረና፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በስህተትና በልምድ፣ እንዲሁም በመመልከት መልክ እየያዘ የመጣ ነው።

ስለሆነም አዳም ስሚዝ ያዳበረው የገበያ ኢኮኖሚ ክንውንና ዕድገት የሚታይ ነገሮችን በሚገባ በመቃኘቱ ብቻ ነው። አዳም ስሚዝ በሁሉም መስክ የሚገለጽ ከፍተኛ ምሁራዊ እንቅስቃሴ በሚታይበትና የኢንዱስትሪ አብዮት በሚካሄድበት ዘመን በ 18 ኛው ክፍለ-ዘመን የተወለደና የኖረ በመሆኑ የገበያን ኢኮኖሚ ዕድገትንና የየግለሰቦችን ታታሪነት ጠጋ ብሎ በመመልከቱ „***The Wealth of Nations***" ብሎ የሰየመውን መጽሀፉን መጻፉ ይህን ያህልም የሚያስደንቅ አይደለም። በሌላ ወገን ደግሞ በ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን የተወለደውና ያደገው ጀርመናዊው ካርል ማርክስ ከሰላሳ ዐመታት በላይ የካፒታሊዝምን ዕድገት ጠጋ ብሎ ከመረመረና ካጠና በኋላ የደረሰበት ድምዳሜ ካፒታሊዝም ውስጣዊ ህጎች ያሉት ብቻ ሳይሆን፣ ደረጃ በደረጃ የሚያድግና

በቀውስም ሊገለጽ የሚችል ስርዓት እንደሆነ አመልክቷል። በሱ ዕምነትም ማንኛውም ስርዓት ታሪካዊ እንደመሆኑ መጠን፣ ካፒታሊዝም ለዝንተ-ዓለም የሚቆይ ስርዓት ሳይሆን ውስጡ ባለው ቅራኔ ሊዳከም እንደሚችልና በሌላ ስርዓት እንደሚተካ አረጋግጧል። ስለሆነም ካፒታሊዝም ከታች ከተራ የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት በመነሳት ቀስ በቀስ እያለ ወደ ተወሳሰበ የአመራረት ዘዴና የሀብት ክምችት በመሸጋገር በአገር ደረጃ ብቻ መወሰኑን አቁሞ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ሊወስድ እንደሚችልም አመልክቷል።

የገበያ ኢኮኖሚ ወይም ካፒታሊዝም በአንዳች ዐይነት ኃይል በራስ ፍላጎት ከላይ ወደ ታች የሚወረወር ስርዓት ሳይሆን ቀስ በቀስ ኢቮሉሺነሪ በሆነ መንገድ የሚያድግና የሚስፋፋ ነው። ስለሆነም ካፒታሊዝም ሊያቆጠቁጥ የቻለው በፊዩዳሉ ስርዓት ሲሆን፣ እያደገና እየተስፋፋ ሲመጣ አዳዲስ የህብረተሰብ ኃይሎችን በመፍጠርና የአረጀውን በመጋፋት የበላይነትን የተቀዳጀ ስርዓት ነው። ስርዓቱም በኢኮኖሚ ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን፣ በህብረተሰብአዊ፣ በፖለቲካ፣ በርዕዮተ-ዓለምና በባህል የሚገለጽ በዐይነት ከፊዩዳሉ ስርዓት የሚለይና ከፍተኛ ውስጠ-ኃይል(Dynamism) ያለው ነው።

ያም ሆነ ይህ በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ መገበያያ ቦታ ወይም አንዳች ዐይነት የገበያ ኢኮኖሚ መኖሩ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም ሁሉም ሰው ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ብቻውን ስለማያመርትና በአንድ ህብረተሰብ ውስጥም የስራ-ክፍፍል እንደመኖሩ መጠን የግዴታ ይህ ዐይነቱ የስራ-ክፍፍል በንግድና እንዲያም ሲል በገንዘብ አማካይነት የሚገለጽና የሚካሄድ ይሆናል ማለት ነው።

የገንዘብ ዕድገትም ከስራ-ክፍፍል መዳበርና ከገበያ ዕድገት ጋር እንደየሁኔታው እያደገና እየተወሳሰበ የመጣ ነው። በመጀመሪያ አንድን የፍጆታ ዕቃ በሌላ ዐይነት መለወጥ የተለመደ ሲሆን፣ ይህ ዐይነቱ ልውውጥ አመቺ ባለመሆኑ በሁሉም ገበያተኛ ተቀባይነት ያለው አንድ የሁሉም ዕቃዎች መለኪያ ወይም መመዘኛ የሆነ ገንዘብ አስፈለገ።

ከአንድ የዕቃ ዐይነት ተነስቶ፣ ከመዳብና ከነሃስ፣ ከዚያም በኋላ ከብርና ከወርቅ የተሰራ የንጉሶች ስዕልና ማህተም ያለበት የቀለጠ ብርና ወርቅ እንደገንዘብ በማገልገል ለገበያ ዕድገት መልክ ሰጥተውታል። ወርቅና ብር እያደገና እየተወሳሰበ ከመጣው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጋር ለመጓዝ ባለመቻላቸውና በጊዜው እንደልብ የሚገኙ ስላልነበር በወርቅ የተደገፈና የመንግስታት ማረጋገጫነት ያለው የወረቀት ገንዘብና ሳንቲሞች እየታተሙ መገበያያ መሳሪያዎች መሆን ቻሉ። በተለይም በ 18 ኛው ክፍለ-ዘመን በእንግሊዝ አገር የኢንዱስትሪ ምርት ሲያድግና የንግድ ልውውጥ ሲስፋፋ ወርቅና ብርን በብዛት አትሞ በኢኮኖሚው ውስጥ ለማሽከርከር አልተቻለም።

ወርቅና ብር(Silver) የተፈጥሮ ሀብቶች በመሆናቸውና እንደልብም ስለማይገኙ በገበያ ላይ በየጊዜው የገንዘብ እጥረት ይከሰት ነበር። ይህንን ሁኔታ ጠጋ ብለው የተመለከቱ የተገለጸላቸው ምሁሮች የመጣላቸው ሃሳብ በወርቅ የሚደገፍ የወረቀት ገንዘብ እያተሙ ማቅረብ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን በመረዳት ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝ አገር የመንግስት ዋስትና ያለበት የወረቀት ገንዘብ በማተም በኢኮኖሚው ውስጥ ማፍሰስ ጀመሩ። የወረቀት ገንዘብ በእርግጥም አመቺና ከሁኔታው ጋር የሚጓዝ በመሆኑ የኢንዱስትሪ ምርትንና ንግድን ማፋጠን ተቻለ። ሌሎች አገሮችም ከእንግሊዝ በመማር በመንግስት የሚደገፍና ወርቅ የጀርባው አጥንት የሆነ የወረቀት ገንዘብ በማተም የኢኮኖሚ ዕድገትን ማፋጠን ቻሉ።

ዛሬ የምናየው የተለያየ የገንዘብ ዐይነት የረጅም ጊዜ የገበያ ዕድገት ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ልዩነቱ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ ሰፋ ባለ የማኑፋክቸር እንቅስቃሴና ሰፋ ባለና ግልጽ በሆነ የገበያ ኢኮኖሚ መደገፉ ለገንዘብ ጠንካራነት ተቀባይነት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ማለት ይቻላል። የማኑፋክቸር እንቅስቃሴ ባልተስፋፋባቸው፣ የውስጥ ገበያ ባልዳበረባቸው፣ የምርት ክንውን በሳይንስና

በቴክኖሎጂ በማይደገፍበት፣ ከተማዎችና መንደሮች ለሰው መኖሪያ ሆነው በደንብ ባልተገነቡበት፣ እነዚህም በተለያዩ የመመላለሻ መንገዶች ባልተሳሰሩበት በየአገሮች ውስጥ የሚሽከረከረው ገንዝብ ጥንካሬነት የለውም።

በተጨማሪም ለአንድ አገር የገንዘብ መጠንከር አብዛኛው ህዝብ ተቀጥሮ የሚሰራና፣ በሚያገኘው የወር ደሞዝ ማንኛውንም ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ገዝቶ የሚጠቀም ከሆነ የገንዘብ መሽከርከር ፍጥነት(Velocity of Money) መጨመር ለገንዘብ መጠንከር ዋናው ምክንያት ይሆናል። በሌላ ወገን ግን የሁሉም አገሮች የወረቀት ገንዘቦች ውስጣዊ ዋጋ(Intrnisic Value) የላቸውም። ለምሳሌ አይሮ ከጥጥ ሲታተም፣ ሌሎች አገሮች ደግሞ በቀላሉ ሊቀደድ ወይም በአየር ጠባይ መለዋወጥ የተነሳ ሊበላሽ ከማይችል ፖልይሜር ከሚባል ልዩ ዐይነት የኬሚካል ውጤት የሚታተም ገንዘብ ነው። ከህትመት ዋጋ ጉዳይ አንዳንዶች ጠንከር ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊበላሹ ወይም ሊቀደዱ ይችላሉ።

ከዚህ ስንነሳ የአሜሪካን ዶላርና አይሮ ታሪካዊ እንጂ ዘለዓለማዊ አይደሉም። ከራሳቸው አገሮች አልፈው ለሌላ አገር የውስጥ ገበያ ዕድገትና ለኢኮኖሚው መተሳሰር አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ አይችሉም። የሁሉንም ኢንዱስትሪ አገሮች ዕድገት ስንመለከት፣ በመጀመሪያ እንግሊዝ የወረቀት ገንዘብ በማተም ነው የኢንዱስትሪ ዕድገትንና የውስጥ ገበያን ማስፋፋት የቻለችው።

እንዲሁም የአሜሪካ ዶላር የዓለም ንግድ መገበያያ ገንዘብ ከመሆኑ በፊት በመታተምና በክሬዲት ሲስተም በመሰራጨት ነው በኢንዱስትሪና በቴክኖሎጂ ምጥቀትን ሊያገኝ የቻለው። በጊዜው የጆርጅ ዋሽንግተን የገንዘብ ሚኒስተር የነበረው አሌክሳንደር ሃሚልተን የመንግስት ሴኩሪቲ በማተምና ገንዘብ ካላቸው ገንዘብ በመበደር ነው በማኑፋክቸር ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪ አብዮት ማካሄድ የቻለው።

ጀርመንም በተለይም ከእንግሊዝ በመማርና የራሷን የባንክ ሲስተም በማቋቋምና የክሬዲት ስርዓት በመፍጠር ነው ቀስ በቀስ የኢንዱስትሪ አብዮት ያካሄደችውና በአንድ ትውልድ ጊዜ ውስጥ እንግሊዝን በቴክኖሎጂ ቀድማ መሄድ የቻለችው። ይህ ሁሉ የሚያረጋግጠው ከሌሎች ነገሮች ጋር በመደመር ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ዋናው አንቀሳቃሽ ኃይል ዶላርና አይሮ ወይም ሌላ የውጭ ገንዘብ ሳይሆን የአንድ አገር ገንዘብ ብቻ ነው። በተጨማሪም አንድ አገር ከውጭ አገር በመበደር ሰፋ ያለና ስርዓት ያለው፣ እንዲሁም በሳይንስና በቴኮኖሎጂ የተመሰረተ የካፒታሊስት ወይም የገበያ ኢኮኖሚ ያዳበረበት አገር የለም።

በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተቋቋመው የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ የሚያረጋግጠው ዕዳ(International Debt) የየአገሮችን ሀብት መምጠጫ ወይም መዝረፊያ መሳሪያ በመሆን ለኋላ-ቀርነት ወይም ግልጽ ለሆነ፣ በስራ-ክፍፍል ላይ ለተመሰረተ የገበያ ኢኮኖሚ አለማደግ ዋናው ምክንያት እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የንግድ መለዋወጫ ገንዘብ የእንግሊዝ ፓውንድ ሲሆን፣ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ደግሞ ዶላር የዓለም ንግድ መገበያያና የሀብትም ማጠራቀሚያ ገንዘብ ሊሆን ችሏል። ፓውንድና ዶላር የዓለም ንግድ መገበያያ ገንዘብ ብቻ ሳይሆኑ የበላይነትን መግለጫና ማረጋገጫ መሳሪያዎችም ናቸው። ስለሆነም የደካማ አገሮችን የጥሬ-ሀብት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ለመሆን በቅተዋል።

ለምሳሌ እንግሊዝ ኃያል መንግስት እስከነበረችበት እስከ 1930 ዎቹ ዓመታት ድረስ ፓውንድ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት የነበረው የንግድ መለዋወጫ ገንዘብ ነበር። እንግሊዝ የበላይነቷን በአሜሪካን ስትነጠቅ በ 1944 ዓ.ም በብሬተንስ ውድስ ስምምነት ላይ የእንግሊዙ ተወካይ የነበረው ኬይንስ አንድ ከሁሉም አገር ነፃ የሆነ፣ በተለያዩ አገሮች ከረንሲዎች የሚደገፍ „ባንኮር" የሚባል አርቲፊሻል ገንዘብ የንግድ መለዋወጫ መሆን አለበት ብሎ ሲከራከር፣ የአሜሪካንን መንግስት ይወክል የነበረው ኋይትስ የሚባለው

እምቢ በማለቱ ዶላር የዓለም ንግድ መለዋወጫና የሀብት ክምችት መሳሪያ ለመሆን በቃ። በጊዜው አሜሪካ ሰፋ ያለ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የሚደገፍ ትልቅ ገበያ ስለነበረው፣ በውጭ ንግድም ትርፋማ በመሆኑና ከሌሎች አገሮችም ጋር ሲወዳደር ብዙ የወርቅ ክምች ስለነበረው ዶላር በዓለም አቀፍ ደረጃ የንግድ መለዋወጫ ገንዘብ መሆን አለበት ብሎ መከራከሩ የሚያስገርም አይደለም።

ያም ሆነ ይህ መሰረታዊው ጥያቄ በሁሉም ማህበረሰቦች ውስጥ የገበያ ኢኮኖሚ ብቅ ቢልምና ቢያድግም ለምድንነው ወደ ካፒታሊዝም ሊለወጥ ያልቻለው ? ለሚለው መመለስና መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው።

ምክንያቱም በተለይም ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች የካፒታሊዝምን አነሳስና ዕድገት መረዳት ከቻሉ በቀላሉ ለራሳቸው የሚስማማ የህብረተሰብ ፕሮጀክት መንደፍ ስለሚችሉ ነው። ይሁንና ግን እዚህ ላይ መዘርዘር አንባቢውን ማስልቸት ብቻ ሳይሆን፣ በተወሰኑ ቃላቶችና በግብዝነት ምክንያቱ እንደዚህ ነው ብሎ በቂ ትንተና ወይም መልስ መስጠት በፍጹም አይቻልም። ስለካፒታሊዝም አነሳስና ዕድገት ሰፊ ሀተታ መስጠት በዚህ አጭር ጽሁፍ ላይ አስፈላጊ አይደለም።

ያም ሆነ ይህ ተራ የገበያ ኢኮኖሚና ካፒታሊዝም አንድ አይደሉም። አብዛኛዎች የዓለም ማህበረሰቦች የገበያ ኢኮኖሚ ቢያዳብሩም ሁሉም አገሮች ወደ ካፒታሊዝም ሊሸጋገሩ አልቻሉም። በአውሮፓ ምድር ከረጅም ጊዜ ጭፍን የሆነ የካቶሊክ ሃይማኖት አገዛዝ በኋላ በተፈጥሮ ሳይንስ፣ በፍልስፍና፣ በህንፃ አገነባብና በስዕል የሚገለጽ የመንፈስ ተሃድሶ(Renaissance)፣ ቀጥሎም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ብቅ ማለትና የካቶሊክን ዶግማ መቀናቀንና ቀጥሎም መስበር፣ ከዚያም በኋላ በሳይንስ የሚገለጽ ሰፋ ያለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ በነፃ ለማሰብ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ።

በዚያው መጠንም ስርዓት ያላቸው ከተማዎች ሲገነቡና የዕደ-ጥበብ ስራ ሲያብብና፣ እነዚህ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር በመዳበል ለካፒታሊዝም መሰረት ይጥላሉ። ይህ ዐይነቱ እንቅስቃሴ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ እንግሊዝ አገር በኢንዱስትሪ አብዮት በመገለጽ ህብረተሰብን በማመሰቃቀልና ከጥንታዊ የአሰራር ስልት በማላቀቅ ቀስ በቀስ ለካፒታሊዝም ስልተ-ምርት መንገዱን ያመቻቻል። ሌሎች አገሮችም የኢንዱስትሪን አብዮት እንደምሳሌ በመውሰድ ኋላ-ቀር ከሆነ የአመራረትና የአኗኗር ስልት በመላቀቅ የቴክኖሎጂ ዕድገትን ያፋጥናሉ። አንዱ ከሌላው በመኮረጅና ሃሳብ ለሃሳብ በመለወዋጥ በተለይም የሃሳብ ፍሰት በቀላሉ ሊስፋፋ በሚችልበት ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ካፒታሊዝም ሊያድግና ሊስፋፋ ቻለ። ስለሆነም ካፒታሊዝም ከተራ የገበያ ኢኮኖሚ በዓይነትም ሆነ በውስብስብነት እጅግ በላቀ መልክ ይለያል።

ባጭሩ ካፒታሊዝም፣

**1** ኛ) በግል ሀብት የሚገለጽ ነው። በተለይም በኢንዱስትሪ ምርት ላይ የሚያተኩር ነው።

**2** ኛ) በኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ መኖር አለበት። የሰው ጉልበት ዋናው የትርፍ ምንጭ ነው።

**3** ኛ) በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚመረተው ምርት በቀጥታ ገበያ ላይ ወጥቶ የሚሸጥ ስለሆነ የዋጋና የወጪ ስሌትያስፈልገዋል። ይህም ማለት ማንኛውም አምራች የሚያመርተው ትርፍ ለማግኘት እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ

**4** ኛ)በአምራቾች መሀከል ውድድር መኖር አለበት። በውድድር አማካይነት ብቻ ነው የቴክኖሎጂ ምጥቀት ሊታይ የሚችለው።

**5** ኛ**)** በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ውስጥና(Interindustry Trade) በጠቅላላው አንድ አገር ኢኮኖሚ ውስጥ የስራ-ክፍፍል መኖር(Intraindustry Trade) ለካፒታሊዝም ዕድገት እጅግ ወሳኝ ነው። በዚህ አማካይነት መተሳሰር ሲኖር፣ዕድገቱም ይፋጠናል።

**6** ኛ**)** የፍጆታ ዕቃዎችን በሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችና በማሺን ኢንዱስትሪና እንዲሁም ኢንዱስትሪዎችን ዲዛይን አድርገው

በሚያቀርቡ መሀከል ግልጽ የሆነ የስራ ክፍፍል መኖር አለበት። በእነዚህ ሁለት ክፍሎች (Department1 & Department II) መሀከል ግልጽ የሆነ የስራ-ክፍፍል ሲኖር ካፒታሊዝም በዐይነትም ሆነ በብዛት ማደግ ይችላል።